የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት

ማዕከላዊ ነጋሪት ጋዜጣ

MAEKELAWI NEGARIT GAZETA

OF THE CENTERAL ETHIOPIA REGIONAL STATE

በማዕለላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት
የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

ጠባቂነት የወጣ

ወልቂጤ 3ኛ ዓመት ቁጥር 12

የካቲት 20 2016 ዓ/ም

Wolkite 3rd Year No 12
February 28/2024

## አዋጅ ቁጥር 12/2016 ዓ.ም
## የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት
## የከተሞች አስተዳደር አዋጅ

### መግቢያ

በክልሉ ከተሞች መልካም አስተዳደር በማስፈን እና ሁሉን አቀፍ ልማት በማረጋገጥ ከተሞች የምርት፣ የአገልግሎትና የገበያ ማዕከላት ሆነው የክልሉን የኢንዱስትሪ ልማት ወደ ከፍተኛ ደረጃ ለማሸጋገር የላቀ አስተዋጽኦ እንዲኖራቸው ማድረግ በማስፈለጉ፣

በክልላችን በሚገኙ ከተሞች ከፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ጋር በተጣጣመ መልኩ ቀልጣፋና ፍትሃዊ ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ማስፈን እና ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበትን የአሠራር ሥርዓ መዘርጋት ለልማት መፋጠንና ለዴሞክራሲ ግንባታ መጠናከር ጉልህ ፋይዳ ያለው በመሆኑ፣

ከከተማነት መስፋፋት አንፃር የከተማ ነዋሪዎችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ያልተማከለ አስተዳደርን ለማጠናከር ከሀገራዊ የከተሞች ፈርጅ መስፈርት አኳያ የክልሉ የከተሞች

## Proclamation no 12 /2024

### A PROCLAMATION FOR THE URBAN ADMINISTRATION OF THE CENTRAL ETHIOPIA REGIONALSTATE

### Preamble

**WHEREAS**, it has become necessary to make urban centers to have high contribution on transforming the industrial development of the region to a higher level being a center of merchandise, services and market by maintaining a good governance and ensuring all rounded development;

**WHEREAS,** maintaining active and fair municipality service, providing and developing working system with clarity and accountability, which is compatible with the rapid growth of a public number of the urban centers found in our region, has high importance for the enhancement of development and democracy building;

**WHEREAS,** it has become necessary to develop organization that reinforce decentralized administration to ensure participation and the

ደረጃ ምደባ መስፈርት እንደገና ማስተካከል እና በከተሞች ያለውን የመልካም አስተዳደር ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል አደረጃጀት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

በተሻሻለዉ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ህገ-መንግስት አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

## ምዕራፍአንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

**ይህ አዋጅ «የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት የከተሞች አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 12/2016» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።**

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ፡-

1."**ሕገ-መንግስት**" ማለት የማዕከላዊ ኢትዮጲያ ክልል ሕገ-መንግስት ነው፣

2."**ክልል**" ማለት የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ነው።

3."**ቢሮ**" ማለት የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ

4."**ከተማ**" ማለት ሁለት ሺህ እና ከዚያ በላይ ነዋሪ ያለው፣ ሀምሳ ከመቶ በላይ ከግብርና ሥራ ውጪ በሆኑ የሥራ መስኮች የተሰማራ ህዝብ የሚኖርበት በሕግ የከተማነት እውቅና የተሰጠው የሕብረተሰብ መኖሪያ አካባቢ ነው፣

5."**ክፍለ ከተማ**" ማለት በሬጂዮፖሊስ ከተማ የከተማ አገልግሎቶችን ለነዋሪው ሕዝብ ተደራሽ ለማድረግ ከከተማ አስተዳደር በታች

benefit of the urban residents in respect of the expansion of urbanization, andregarding tothe criterion of the country urban centers category , to revise the criterion of the regional urban centers grading allocation and to solve the existing problem of good governance in urban centers;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with the sub article 3 of article 55 of the revised constitution of the Central Ethiopia Region State, the following has been Proclaimed.

## CHAPTER ONE

## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "The Urban Administration Proclamation No 12/2024 of the Central Ethiopia Region State."

### 2. Definition

In this Proclamation, unless the context requires, otherwise;

1. "**Constitution**"means the Constitution of the Central Ethiopia Region State"
2. "**Region**" means the Central Ethiopia Region "
3. "**Bureau**" means the bureau of the urban development and constraction
4. "**Urban Center**" means the residential area with two thousands and more residents of which more than fifty percent of the labor forces are engaged in non- agriculture job fields that is granted with accreditation as urban center by law.
5. "**Sub City**" means an entity of a city structure below the city administration and

ከቀበሌያት በላይ የሚዋቀር የከተማ አካል ነው፡
፡

6."**የህዝብ ብዛት**" ማለት በሕግ የከተማነት ዕውቅና በተሰጠው እና በከተማነት በተካለለ አካባቢ የሚገኝ አጠቃላይ የከተማ ነዋሪ ሕዝብ ቁጥር ነው፡፡

7."**ፈርጅ**" ማለት ከተሞች በፖለቲካዊ፣ በኢኮኖሚያዊ እና በማህበራዊ ልማት እንቅስቃሴ ሂደት የደረሱበትን የእድገት ደረጃ ለመመዘን ከተዘጋጁት መስፈርቶች አንጻር ባመጡት ድምር ውጤት መሠረት የተሰጣቸው የከተማነት ደረጃ ነው፣

8."**የከተማ ምክር ቤት**" ማለት በከተማነት በተካለለው አካባቢ በህዝብ ምርጫ የሚቋቋም ህግ አውጪ የመንግስት ሥልጣን አካል ነው፣

9."**ሬጂዮፖሊስ ከተማ**" ማለት የከተሞችን ልማት ከማፋጠን አንፃር የልማት ማዕከል በመሆን በዙሪያቸው ያሉትን ከተሞች ይዘው እንዲያድጉ ለተመረጡ ሰፋፊ ከተሞች የተሰጠ የከተማ ደረጃ ስያሜ ነው፡፡

10. "**የከተማ አስተዳደር**" ማለት ተለይቶ በታወቀ ወሰን የተደራጀ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ልማትና አገልግሎት አሰጣጥን ለመምራት ሥልጣንና ኃላፊነት በህግ የተሰጠው ከተማ ነው፣

11. "**መደበኛ ፍርድ ቤት**" በከተሞች የሚደራጅ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይንም ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፤

12. "**ከተማ ነክ ጉዳዮች አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት**"

above kebeles aims to access urban cervices to resident people in ragiopolis city.

6. "**Population Number**" means a population number of the entire urban center resident found in the area granted with the accreditation of urban by law and bounded as urban.
7. "**Category**" means grading given to urban centers on the basis of cumulative result obtained by urban centers regarding to the prepared criterion to measure the growth standard they achieve in by political, economic and social development activity process.
8. "**Council of the Urban Center**" means entity of the legislative governmental power to be established by the public election in the area bounded as urban center.
9. "**Ragiopolis city**" means an urban level name given to the selected large cities that is developing with the surrounding urban centers being development center regarding to the enhancement of urban centers development
10. "**Urban Center Administration**" means an urban center given power and responsibility bylaw to direct providing of organized political, economical, and social development and service.
11. "**Regular Court**" means the first instant court or high court that to be organized in

ማለት የከተማ ነክ ጉዳዮችን እንዲያይ በከተሞች የሚቋቋም አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ነው፣

13. "**ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት**" ማለት የከተሞችን ነዋሪ ሕብረተሰብ ፍላጎት ከማርካትና ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ችግሮችን ከመቅረፍ አንፃር በሁሉም ከተሞች የሚሰጥ የከተማነክ አገልግሎት ነው፣

14. "**ከንቲባ**" ማለት በከተማው ምክር ቤት የሚመረጥ የከተማውን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች፣ እንዲሁም የመልካም አስተዳደር እና የከተማ አገልግሎት ሥራዎችን በበላይነት የሚመራና የሚያስተገብር የከተማው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ነው፣

15. "**የከንቲባ ኮሚቴ**" ማለት የከተማ አስተዳደር ምክር ቤትነው፣

16. "**ሥራ-አስኪያጅ**" ማለት የከተማውን ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶችን እንዲመራ የሚሰየም የከተማ አገልግሎት ሥራ ኃላፊ ነው፣

17. "**የሕግ ሰውነት**" ማለት በዚህ አዋጅ በከተማነት ለተደራጀ ማህበረሰብ መኖሪያ አካባቢ የሚሰጥ ተቋማዊ ዕውቅና ነው፣

18. "**የከተማ ቀበሌ**" ማለት በከተማ ደረጃ ዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን ነው፣

19. "**ቀጠና**" ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት በከተሞች ሁለንተናዊ የሕዝብ ተሳትፎን ለማሳደግ ከቀበሌ በታች የሚፈጠር የሕዝብ አደረጃጀት ነው፣

the urban centers.

12. **"Administrative Court of the Urban Matters**" means the administrative court to be established in the urban centers to overtake the urban center issues.

13. **"Municipal services**" means urban connected service to be provided in all urban centers regarding to solving social, economic, and environmental problems and satisfying the need of the urban centers resident society.

14. **"Mayor**"means the chief executive of urban center that to be elected by the urban center council and principally directs andsupervises the urban center political, economical, and social matters as well as good governance and the urban center service activities.

15. **'Committee of the Mayor**" means the council of urban center administration.

16. **"Manager''** means a leader that to be appointed to direct the urban center municipality services.

17. **"Legal personality**" means an accreditation of institution given to residence area of the society organized as urban by this proclamation.

18. **"Kebele of the Urban Center**" means a lower administration organ in the urban level.

19. "**Zone**" means a public organization to be created to grow all rounded public participation in the urban centers below

20. "**ሠፈር**" ማለት በከተሞች የህዝብ ልማታዊ ተሳትፎን ለማጎልበት ከቀጠና በታች የሚደራጅ የህዝብ ተሳትፎ አደረጃጀት ነው፣

21. "**ጣቢያ**" ማለት ከሰፈር በታች የህዝብ ልማታዊ ተሳትፎን ለማሳለጥና ለማጎልበት የሚደራጅ የህዝብ አደረጃጀት ነው፣

22. "**የሕዝብ መማክርት ምክር ቤት**" ማለት በከተሞች ቀጠና እና ሠፈር ከሕዝብ የልማት ተሳትፎ አደረጃጀቶች ተወጣጥቶ የሚመሰረት የነዋሪዎች ምክር ቤት ነው፣

23. "**ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ**" ማለት በከተማ ቀጠናዎች የእለት ተእለት ሥራዎችን እንዲያከናውን ከሕዝብ መማክርት ምክር ቤት በበጎ ፈቃድ በተወከሉ አባላት የሚመሰረት ኮሚቴ ነው፣

24. "**የገጠር አገልግሎት ማዕከል**" ማለት በክልሉ የገጠር ቀበሌያት ሥር የሚገኝ በከተማነት ያልታቀፈ ለአካባቢው የተለያዩ አገልግሎቶችን በማቅረብ የገበያ ማዕከል ሆኖ የከተማ–ገጠር ትስስርን በማፋጠን የሚያገለግል ከተማ ቀመስ አካባቢ ነው።

25. "**የከተማ አስተዳደር ወሰን**" ማለት ሥልጣን በተሰጠው አካል የተካለለ እና በከተማው አስተዳደር ሥር የተጠቃለለ አካባቢ ነው።

26. "**የከተማ ፕላን ወሰን**" ማለት ለአንድ ከተማ በከተማ ፕላን መሠረት ለተወሰነ የፕላን ዘመን በካርታ የተካለለ የከተማው የመሬት አጠቃቀም ወሰን ነው።

27. "**ማህበራዊ ፍርድ ቤት**" ማለት እንደ

kebel on the basis of this Proclamation.

20. "**Locality**" means an organization of the public participation to be organized below the sub region of the urban center kebele to promote the public development participation in the urban centers.

21. "**Station**" means a public organization to be organized below a locality to entertain and promote the public development participation.

22. "**Council of the Public Analyst**" means a council of residents to be established from organization of public development participation in the urban center, sub region, and locality.

23. "**Executive Committee**" means a committee to be established by voluntarily delegated member from the council of public analysts to perform daily activity in sub regions of the urban center.

24. "**Rural Service Center**" means an area of the urban touches that accelerate urban rural relationship being market center by providing a various services to the area unbounded to urban center and found under rural kebeles of the region.

25. "**Boundary of the Urban Center Administration**" means an area enclosed under urban center administration and bounded by a body granted with power.

26. "**Boundary of the Urban Center Plan**" means a boundary of the urban center land usage which is bounded by a map for a limited plan year on the basis of the urban center plan.

አስፈላጊነቱ በከተማ ቀበሌ ደረጃ የሚቋቋም የዳኝነት አካል ነው፣

28. "ሰው" ማለት በተፈጥሮ ሰው የሆነ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

### 3. የፆታ አገላለጽ

በዚህ አዋጅ ውስጥ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴት ጾታንም ይጨምራል።

### 4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በክልሉ ባሉት ከተሞች ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ምዕራፍ ሁለት
## የከተሞች ፈርጅ እና ተጠሪነት

### 5. የከተሞች ፈርጅ

1. በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ከተማ ከሚከተሉት የከተማ ፈርጆች በአንዱ ሊመደብ ይችላል።
   ሀ) ሬጂዮፖሊስ፣
   ለ) ፈርጅ አንድ፣
   ሐ) ፈርጅ ሁለት፣
   መ) ፈርጅ ሶስት፣
   ሠ) ፈርጅ አራት፣
   ረ) ፈርጅ አምስት፣
2. የሬጂዮፖሊስ ከተማ ክፍለ ከተማ፣የከተማ ቀበሌ አስተዳደር እና ቀጠና አደረጃጀት ይኖረዋል።
3. ከፈርጅ አንድ እስከ ፈርጅ ሶስት ያሉት ከተሞች የከተማ ቀበሌ አስተዳደር እና የቀጠና አደረጃጀት ይኖራቸዋል።
4. ፈርጅ አራት እና ፈርጅ አምስት ከተሞች የከተማ ቀበሌ አስተዳደር ይኖራቸዋል።
5. የከተሞች ቀበሌ አስተዳደር አደረጃጀት እና ደረጃ

27. **"Social Court"** means a judiciary body to be established in urban Kebele level of the urban center as necessary.

28. **"Person"** means a natural person or a juridical body.

### 3. Gender Reference

In thisProclamation, any expression in gender includes feminine gender.

### 4. Scope of Applicability

This Proclamation shall be applicable in all urban centers found in the region.

## CHAPTER TWO

## Category and Accountability

### 5. Category of the Urban Centers

1. An urban center found in the region may be allocated by one of the following urban center categories;
   a) Ragiopolis
   b) Category one
   c) Category two
   d) Category three
   e) Category four
   f) Category five
2. Ragiopolis city shall have sub-city, kebele administration of the city and organization of the kebele subdivision.
3. Urban centers from category one upto category three shall have kebele administration of the urban center and zonalorganization.
4. Urban centers of category four and five shall have kebele administration of the urban center.
5. Organization and grading of the urban center kebele administration shall be

በደንብ ይወሰናል።

6. በሁሉም ፈርጆች በሚገኙ ከተሞች የህዝብ የልማት ተሳትፎን ለማጎልበት የሠፈር፣ የጣቢያ እና የሕዝብ የልማት ተሳትፎ አደረጃጀቶች ሊኖራቸው ይችላል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

7. በሬጂዮፖሊስ፣ ከፈርጅ አንድ እስከ ፈርጅ አምስት የሚገኙ የከተማ ቀበሌያት በቀበሌ አስተዳዳሪ የሚመሩ ሆነው እንደየደረጃቸው ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት እና የሥራ ክፍሎች ያሏቸው ይሆናሉ።

## 6. የከተሞች ፈርጅ መመዘኛ መስፈርት

1. የከተሞች ፈርጅ እና መመዘኛ መስፈርቶች በደንብ ይወሰናል።
2. በዚህ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የዞን አስተዳደር ማዕከል የሆነ ከተማ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በልዩ ሁኔታ ታይቶ ደረጃው ሊወሰን ይችላል።

## 7. ተጠሪነት

የከተሞች ተጠሪነት በሥልጣን ተዋረድ ደረጃ ላይ የተመሰረተ እና ለየከተማው ነዋሪ ሕዝብ ሆኖ፣

1. የሬጂዮፖሊስ ከተማ እና ከፈርጅ አንድ እስከ ሶስት ያሉት ከተሞች ተጠሪነታቸው ለሚገኙበት ዞን ወይም ልዩ ወረዳ አስተዳደር ይሆናል።
2. የፈርጅ አራት እና ፈርጅ አምስት ከተሞች ተጠሪነታቸው ለሚገኙበት ልዩ ወረዳ ወይም ወረዳ አስተዳደር ይሆናል።

## 8. በከተማነት ስለመቋቋምና እውቅና ስለማግኘት

1. ማንኛውም ማህበረሰብ መኖሪያ አካባቢ የከተማነት

defined by regulation.

6. Urban centers found in all categories may have locality, post and the public development participation organizations promote the public development participation. The detail shall be defined by regulation.
7. The urban center kebeles found in ragiopolis and urban centers from category one up to category five shall be directed by the kebele administrator and shall have municipality services and work division as their standard.

## 6. Evaluating Criterion for the Categories of the Urban Centers

1. The urban centers categories and the ruling criteria shall be defined by regulation.
2. Without prejudice to the provision in this article, the grading of the urban center of zonal administration center may be determined by especial consideration of the regional administrative council.

## 7. Accountability

The accountability of urban centers shall be to the urban center resident people based on the level of the power hierarchy, and

1. The Urban centers from category one upto category three shall be accountable to the zone or especial woreda administration they are found in.
2. Urban centers of category four and five shall be accountable to the especial woreda or woreda administration they are found in.

## 8. Establishment and Accreditation

1.Every community residential area shall be

እውቅና ሊያገኝ የሚችለው ቢሮው በከተማነት ሲያቋቁመውና እውቅና ሲሰጠው ብቻ ነው፡፡

2. የከተማነት እውቅና ማግኘት የሚቻለው ማህበረሰቡ ለቢሮው በሚያቀርበው ጥያቄ ወይም ቢሮው በራሱ ተነሳሽነት የከተማነት እውቅና በማጥናት በሚሰጠው ውሳኔ ነው፡፡
3. ቢሮው ማመልከቻውን በተቀበለ እስከ ስድስት ወራት ባለው ጊዜ ውስጥ ጥናቱን አጠናቆ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ምላሽ ያላገኘ ማንኛውም የማህበረሰብ መኖሪያ አካባቢ ለበላይ አካል ጥያቄውን ማቅረብ ይችላል፡፡

5. አንድ ማህበረሰብ መኖሪያ አካባቢ የመገኛ ስፍራው በሁለት ወረዳዎች አስተዳደር ወሰን ላይ ከሆነ ተጠሪነቱ የሚወሰነው ሁለቱም ወረዳዎች ተጠሪ በሆኑለት የዞን አስተዳደር ምክር ቤት ሲሆን በሁለት ዞኖች ወይም ልዩ ወረዳዎች አስተዳደር ወሰን ውስጥ ከሆነ ተጠሪነቱ የሚወሰነው በክልል መስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል፡፡

## 9. የሕግ ሰውነት ስለማግኘት

በዚህ አዋጅ መሰረት የከተማነት እውቅና የተሰጠው የማህበረሰብ መኖሪያ አካባቢ፣

ሀ) የራሱ የህግ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ በዚያ ስም የመጠራት፣

ለ) ውል ለመዋዋል፣የንብረት ባለቤት ለመሆንና ንብረቱንም ለማስተዳደር፣ ለመክሰስና ለመከሰስ የህግ ችሎታ ይኖረዋል፡፡

## 10.የሕግ ሰውነትን ስለመሠረዝ

1. የከተማ የሕግ ሰውነት ሊሠረዝ የሚችለው

able to attain the urban accreditation only where the bureau establishes it as urban center and grants accreditation.

2. An urban center accreditation could be acquired where the bureau determines based on study by its own initiation or up on the request of the community.
3. The bureau must respond by completing study within six months from accepting application.
4. According to the sub-article 3 of this article, any unresponded community residence area may present its appeal to the principal body.
5. If the foundation place of the community residence area is on the boundary of the two woreda administration , the accountability shall be to zonal administration council that the two woredas accountable to and if it is in the boundary of two zones or especial woredas administration , its accountability shall be determined by the regional executive council.

## 9. Aquiring Legal Personality

The community residence area that granted with accreditation of urban center:-

a) Shall be designated to that name being a body having its own legal personality.

b) Shall have a legal ability to conclude contract, to be property owner and to administer the property, to sue and to be sued.

## 10. Cancellation of Legal Personality

1. The urban center legal personality shall be

የተሰጠውን የህጋዊ አካልነት ዕውቅና ጠብቆና የከተማነት መስፈርቶችን አሟልቶ መቀጠል ሲሳነውና በቢሮው ሲወስን ይሆናል።

2. የከተማው ሕጋዊ ሰውነት ከመሠረዙ በፊት የተገኙ መብቶችና ግዴታዎች ከተማው ተጠሪ ለሆነለት አስተዳደር አካል ይሸጋገራሉ።

## 11. የከተማ ስም ለውጥ ስለማድረግ

1. የአንድ ከተማ ስም ለውጥ ማድረግ የሚቻለው በከተማው ነዋሪዎች የተደረሰው ስምምነት በከተማው ምክር ቤት፣ ከተማው ተጠሪ በሆነለት የአስተዳደር እርከን ወይም መስተዳድር ምክር ቤት ተቀባይነት ሲያገኝ ነው። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።
2. ኩታ ገጠም የሆኑ ከተሞች በነዋሪዎቻቸው ስምምነት መሰረት ተዋህደው በአንድ ስም ሊጠሩ ይችላሉ፣
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የከተሞቹ ውህደት ሁለቱ ከተሞች ተጠሪ ለሆኑለት አስተዳደር ምክር ቤት ውሳኔ የተደገፈ መሆን ይገባዋል፣
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት የስም ለውጥ የተደረገ እንደሆነ በቀድሞ ስም የተገኙ መብቶችና ግዴታዎች ወደ አዲሱ ስም ይሸጋገራሉ።

## 12. ስለከተማ አስተዳደር አካላት

1. የከተማ አስተዳደር ከተሞች በስራቸው የተለያዩ ተቋማት ይኖሯቸዋል፦
2. በዚህ አንቀጽንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በከተማው የሚቋቋሙት ዋና ዋና አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች፣ በጽ/ቤቶች፣ በአገልግሎትና በዩኒት ተቋማትና መሰል ተቋማት ሊደራጁ ይችላሉ። ዝርዝር በደንብ ይወሰናል።
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 የተመለከተው

cancelled when it is unable to countinou the given accreditation of legal personality and unable to persist on completing the urban criterion;

2. Rights and duties acquired before the cancellation shall be transferred to the administration that the urban center accountable to.

## 11. Altering Designation of the Urban Center

1. Altering Designation of urban center shall be possible where the agreement made by the urban center residents is accepted by the urban center council, the administration stage that the urban center accountable to executive council. The detail shall be defined by regulation.
2. The urban centers adjacent may be combined and called by a common name on the basis of the residents agreement.
3. Without prejudice to the expression on the sub-article 2 of this article the combination of the two urban centers should be supported by the decision of administration council that the urban centers accountable to.
4. Where the designation is alterd on the basis of sub-article 1 and 2 of this article the aquired rights and duties with the former designation shall be transferred to the new.

## 12. Urban Centre administrative bodies

1. City administration urbans shall have different institutions under them;
2. Subject to the provisions of sub-paragraph 1 of this article, the main executive offices established by the city may be organized into offices, services, units, and similar institutions. List is

እንደተጠበቀ ሆኖ በከተሞች የአስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ በክላስተር ሊደራጁ ይችላሉ፤

## ምዕራፍ ሦስት
## የከተሞች ሥልጣንና ተግባር

### 13.የከተሞች ሥልጣን እና ተግባራት

1. የክልሉ ከተሞች በዚህ አዋጅ ተለይተው በተሰጧቸው ጉዳዮች ላይ የሕግ አውጪነት፣ የሕግ አስፈጻሚነት እና የዳኝነት ስልጣን አላቸው።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከተሞች ከዚህ በታች በዝርዝር የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሯቸዋል።

ሀ) ራዕዩን፣ ዓላማውን እና ተግባራቱን እንዲሁም አግባብነት ያላቸውን የአፈፃፀም ስልቶችን ይወስናል፣ተግባራዊ ያደርጋል፣

ለ) የሀገሪቱን፣ የክልሉን ሕጎች እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው አካላት ያወጧቸውን ሕጎች የማይቃረኑ አካባቢያዊ ሕጎችን ያወጣል፣ በጉዳዮቹ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣ ልማትና ልማታዊ መልካም አስተዳደር ያሰፍናል፣ ያረጋግጣል፣

ሐ) በክልሉ ሕግ መሰረት የራሱን በጀት ያስተዳድራል፣

መ) የክልሉ መንግስት በሚያወጣው የፋይናንስ ህግ መሠረት የከተማውን ገቢ ምንጭ ይወስናል፣ ግብር፣ ታሪፍ እና የአገልግሎት ክፍያ ያሻሽላል፣ ያሰፋል፣ ይሰበስባል፣ ለከተማው ልማት ያውላል አግባብ ያለው አካል ሲፈቅድ ብድር ይበደራል፣

ሠ) ከተሞች አግባብ ያለው አካል እንዲያውቀ

well determined.

3. Subject to sub-paragraph 2 of this article, executive offices in cities may be organized in clusters as needed;

## CHAPTER THREE

## Powers and Duties of the Urban Centers

### 13. Powers and Duties of the UrbanCenters

1) Theurban centers shall have the legislative, executive and judiciary power on the matters identified and given to them by this Proclamation.
2) Without prejudice to the general provision of sub –article1 of this Proclamation, the urban centers shall have powers and duties indicated blow in detail;

a) Determine the vision, goal and the duties as well as the relevant performance systems; impliment the same provision.

b) Enact local laws to be consistent with the country, regional and others laws enacted by concerned bodies , provide decision on the matters, maintain and ensure development and developmental good governance;

c) Administer thier own budget on the basis of the regional law.

d) Shall determine the urban center income on the basis of financial law to be issued by the region government; improve, expand and collect tax, tariff and the service payment; invest on the urban center development; credit loan when permitted by the relevant body.

e) Establisha sisterly relationship with

በማድረግ ከሀገር ውስጥና ከውጪ ሀገር ከተሞች ጋር እህትማማች ግንኙነት ይፈጥራል፣ በዚህ አዋጅና በሌሎች ሕጎች መሰረት ስምምነት ያደርጋል፣

ረ) ለሕዝብ አገልግሎት አስፈላጊ በሆነ የከተማ ይዞታ ላይ ለሰፈረው የግል ንብረት በሕግ መሰረት በቅድሚያ ተመጣጣኝ ካሳ በመክፈል ለሕዝብ አገልግሎት እንዲውል ያደርጋል፣

ሰ) የነዋሪውን ፍላጎት በሚያሟላ መልኩ ስታንዳርዱን የጠበቀ ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት ያቀርባል፣ መቅረቡንም ያረጋግጣል፣

ሸ) ሰላምና አስተማማኝ ፀጥታ የሰፈነበት የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታን የሚያጠናክር የግሉ ሴክተር፣ የሲቪክ ማሕበራት እና የሕዝብ ልማታዊ ተሳትፎ እንዲጎለብት ያደርጋል፣

ቀ) በከተሞች የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥና የኢኮኖሚ አቅም ለማሳደግ የሚያስችሉ ፕሮግራሞች ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣

በ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የከተማውን ፕላን ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣

ተ) የከተማ ፕላን ዝግጅቱና አተገባበሩ ቢያንስ የ30፣ 30 እና 40 ምጣኔ መርህን ያገናዘበ መሆኑን ያረጋግጣል፣፣ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

ቸ) ከተሞች በተቀናጀ መሠረተ ልማትና ፕላን እንዲመሩ ያደርጋል፣የውሃ፣የመብራት፣የስልክ አቅርቦትን ያመቻቻል፣

ኀ) የከተሞችን የአስተዳደርና የፕላን ወሰን ይለያል፣ ከሚመለከታቸው መንግስታዊ አካላት ጋር ያካልላል፣ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል::

domestic and overseas urban centers up on perior notice to concerned body; conclude contract on the basis of this Proclamation and others laws.

f) Effect the private property situated on the urban center land, necessary for the public service, to be for the public service by paying a reasonable compensation in advance on the basis of law.

g) Provide the standardized municipality services in a way that satisfy the need of the residents; ensure the provision of the same.

h) Overtake the private sector, civic society and the public development participation to be grown which in turn reinforce building the democratic system based on peace and the ensured security.

i) Develops and implements programs to ensure food security and increase economic capacity in cities.

j) Prepare and implement the urban center plan with the collaboration of the concerned bodies.

k) Confirm if the urban center plans, preparation and implementation take into consideration at least the 30, 30 and 40 economic principle; the detail shall be defined by regulation.

l) Overtake urban centers to be directed by integrated infrastructure and plan; facilitate water, electricity, and telephone supply.

m) Identify the administration and the plan

ነ) ማናቸውም ግንባታዎች አግባብነት ያለውን ሕግ የጠበቁ እና የከተማውን፣ የአካባቢውንና ማህበራዊ ደህንነት እንዲሁም ውበት በጠበቀ መልኩ፣ የከተማውን መሪ ፕላን መስፈርቶች ተከትለውመገንባታቸውንይከታተላል፣ያረጋግጣል፣

ኘ) በክልሉ መንግስት የቤት ልማት ፖሊሲ መሠረት የከተማውን ነዋሪዎች የቤት ልማት ፍላጎት ለሟሟላት ጥረት ያደርጋል፣ የቤት ልማት ሥራዎችን ይመራል፣ ይተገብራል፤

አ) ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል የከተማ መሬት ያዘጋጃል፣ የለማ መሬት ያቀርባል፣ መሬት ነክ መረጃ ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፣

ከ) የአረንጓዴ ልማት ያስፋፋል፣ ለሕብረተሰቡ የመዝናኛ እና መናፈሻ አገልግሎት እንዲቀርብ ያደርጋል፣ የፍሳሽና ደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሥርዓት ይዘረጋል፣ የጎርፍ አደጋ ሥጋትን ይከላከላል፣

ኸ) የደን ተከላ፣ የአፈር እና የዱር እንስሳት ልማት የመሳሰሉ የከተሞች አካባቢ ጥበቃ ተግባራትን ያከናውናል፣ መከናወናቸውን ያረጋግጣል፣

ወ) የቄራ፣ የአንቡላንስ እና እሳት አደጋ አገልግሎቶች እንዲሰጡ ያደርጋል ፣ የዘላቂ ማረፍያ አገልግሎቶችን ያመቻቻል፣ያቀርባል፣

ዐ) የነዋሪዎች አድራሻ በቀላሉ የሚገኝበትንና ሕብረተሰቡ የተለያዩ አገልግሎቶችን ያለችግር የሚያገኙበትን ዘመናዊ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣

ዘ) በከተማ ውስጥ የሚካሄዱ የንግድ ሥራዎች የመንግሥት ሕጎችንና ደንቦችን በተከተለ አግባብ መከናወናቸውንና ደረጃቸውን የጠበቁ ምርቶችና

boundary of the urban centers; demarked it with the concerned government bodies; the detail shall be defined by regulation.

n) Follow up and ensure if every construction is built inline with the pertinent law and in line with the urban center environment, social security as well as beauty, constructed following the criteria of the urban center master plan.

o) Maintain effort to satisfy the demand of the house development of the urban center residents on the basis of the house development policy of the regional government; direct and implement the house development activities.

p) Develop the urban center land for various services; supply the developed land; administer and organize land connected information.

q) Expand the green development, effect the entertainment and recreation service to be supplied to the society; develop the system for handling or disposal of runny or solid waste; prevent the flood disaster risk.

r) Perform the urban centers environment protection activities similar to afforestation, the soil, and wildanimal's conservation; approve if they are implemented.

s) Effect the abattoir, ambulance and the fire brigade force services to be provided; facilitate and provide the services of stable settlement.

t) Develop the modern process system in which the residential address to be detected

አገልግሎቶች ለተጠቃሚው ህብረተሰብ መቅረባቸውን ይከታተላል፣ያረጋግጣል፣

ዠ) ለባለሀብቶች ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ኢንቨስትመንትን ያስፋፋል፣

የ) በከተሞች የቱሪስት መስህቦች እንዲደራጁ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች እንዲጠበቁ ያደርጋል፣

ደ) ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት በከተሞች እንዲስፋፋ ያደርጋል፣

ጀ) መከላከልን መሰረት ያደረገ የጤና ጥበቃ አገልግሎት ያስፋፋል፣ ነዋሪው ሕብረተሰብ ከተለያዩ ወረርሽኞችና ተላላፊ በሽታዎች መጠበቃቸውን ያረጋግጣል፣

ገ) የወጣቶች ማዕከላት፣ የስፖርት ማዘወተሪያ ስፍራዎችና የህዝብ ቤተመጻሕፍት እንዲስፋፉ ያደርጋል፣

ጠ) የከተማ ነዋሪዎችን ልማታዊ ተሳትፎ ያሳድጋል፣ በተለይም የወጣቶችንና የሴቶችን ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ያጠናክራል፣ ያረጋግጣል እንዲሁም አረጋዊያን፣ አካል ጉዳተኞች እና አሳዳጊ የሌላቸው ህፃናት እንክብከቤ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

ጨ) የከተማውን ስትራቴጂክ እቅድ፣ የልማት ፕሮግራሞችንና ፕሮጀክቶች ዝግጅትና ትግበራውን ይከታተላል፣

ጸ) የከተማው የትራንስፖርት አገልግሎት ያዘምናል፣ ለነዋሪዎች ፍትሃዊ አገልግሎት መስጠቱን ያረጋግጣል፣

ጻ) በከተማው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ ሥርዓት መዘርጋቱንና መተግበሩን ያረጋግጣል፣

ፀ) ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ተግባራት ያከናውናል፡፡

easily so as the society obtain various services without problem.

u) Follow up and approve if the trade activities practiced in the urban center are performed according to the government laws and regulations, and the standardized products and services are provided to the beneficent society.

v) Expand investment by creating conducive condition for the investors.

w) Affect the tourist attractiveness to be organized in the urban centers, historical and traditional heritages to be protected.

x) Overtake quality education to be expanded in the urban centers.

y) Expand the health care services based on prevention; approve if the resident society are protected from various invading and transmitted diseases.

z) Overtake the youth centers such as sport practicing places and public library to be expanded.

aa) Enhance the developmental participation of the urban residents, strengthen and ensure especially the participation and benefit of youths and females; facilitate the condition in which elderly, handicaps and orphanage obtain care.

bb) Follow up the participation and implementation of the urban centers strategic plan the development programs and projects.

cc) Modernize the transportations of the urban center; ensure the provision of fair service

3. በመንግስት ሰራተኞች አስተዳደር ህግ መሰረት ሰራተኞቹን ያስተዳድራል፣
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር የተዘረዘሩትን ተግባራትና አገልግሎቶችን በተቀላጠፈ መንገድ ለማቅረብ ማንኛውም ከተማ አመቺ ሆኖ ሲገኝ ከመንግስት፣ ከግሉ ሴክተር ወይም ከበጎ ፈቃደኛ ድርጅቶች ጋር ውል ይገባል እንዲሁም የህዝብ ልማት ተሳትፎ አደረጃጀቶችን ይፈጥራል፣
5. እያንዳንዱ ከተማ ሥነ-ሥርዓትና ደንብ አስከባሪ አካል ሊያደራጅ ይችላል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

## ምዕራፍ አራት

## የከተሞች የመንግስት የሥልጣን አካላት

### 14. በከተሞች የመንግስት የሥልጣን አካላት

1. በሬጂዮፖሊስ፣ ከፈርጅ አንድ እስከ ፈርጅ ሶስት ከተሞች የሚከተሉት የመንግስት ሥልጣን አካላት ይኖሩታል፣

   ሀ) የከተማ ምክር ቤት፣

   ለ) የከንቲባ ኮሚቴ፣

   ሐ) መደበኛ ፍርድ ቤት፣

2. በፈርጅ አራትና ፈርጅ አምስት ከተሞች የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፣

   ሀ) የከተማ ቀበሌ ምክር ቤት፣

   ለ) የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት፣

to the residents.

dd) Ensure if the registration system of the vital events developed and implemented in the urban center.

ee) Perform others relevant activates,

3) Administer employees on the basis of the public service's law.
4) Every urban center concludes contract in favorable condition with government, private sector or charity organization to provide activates and services listed under sub-article 2 of this article actively and to create organizations of the public development participation.
5) Each urban center may organize a body supervise system and regulation; the detail shall be defined by regulation.

## CHAPTER FOUR

## Governmental Power Organs in the Urban Centers

### 14. Power Organs of the Government in the Urban Centers

1) In the ragiopolis and urban centers from the category one up to category three shall have the following governmental power organs;
   a) Council of the urban center,
   b) Committee of the mayor,
   c) The ordneryCourt
2) The urban centers of categories four and five shall have the following organs;
   a) Council of the kebele urban center,
   b) Council of the kebele administration

ሐ) ማሕበራዊ ፍርድ ቤት፣

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 እንደተጠበቀ ሆኖ ከተሞች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 44 መሠረት የከተማ ነክ ጉዳዮች አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ሊኖራቸው ይችላል።

## 15. ስለከተማ ምክር ቤት

1. የከተማ ምክር ቤት ምርጫ በብሔራዊ የምርጫ ሕግ መሠረት ይከናውናል።

2. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የየከተማውን የሕዝብ ብዛትና የምርጫ ጣቢያዎችን መሠረት በማድረግ የከተማ ምክር ቤቱን አባላት ብዛት ይወስናል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) በከተማው ውስጥ የሚኖረው የአካባቢው ብሔሮች ወይም ብሔረሰቦች ቁጥር አብላጫ በማይሆንበት ጊዜ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ከዞን ወይም ከልዩ ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ጋር በመመካከር ከከተማው ክልል ምርጫ በተጨማሪእስከ 30% ያለውን የከተማውን ምክር ቤት መቀመጫ ለከተማው አካባቢ ብሔሮች እና ብሔረሰብቦች እንዲመደብ ያደርጋል።

ለ) በንዑስ አንቀጽ 3 (ሀ) ሥር የተጠቀሱት ተወካዮችን መምረጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አዋሳኝ ከሆኑ ለክልልና ለዞን በምርጫ አሸንፈው ከተመረጡ ተወካዮች ከአካባቢው ብሔሮች እና ብሔረሰቦች ለከተማ ምክር ቤት ሊሰይም ይችላል።

c) Social court,

3) Without prejudice to the sub article 1 and 2 of this article, urban centers may have administrational court of the urban connected matters on the basis of article 44 of this Proclamation.

## 15. Council of the Urban Center

1. Election of the urban center council shall be implemented in accordance with the national electoral law.
2. The administrative council of the region shall determine the number of the urban center council members based on the size of population andpolling stations of each urban center.
3. Without prejudice to the provision in the sub-articles 2 of this article:-
   a) The administrative council of the region shall effect up to 30% of the urban center council seat to be allocated by urban area nations and nationalities in addition to the election of the urban region by discussing with zone or especial woreda administration council unless the locality nations or nationalities in the urban center become the majority .
   b) When electing the representative mentioned under sub-article 3a is found necessary, the urban center may assign to the council from representatives elected winning the regional and zonal election that are neighbors and beingthe nations and nationalities of the locality.

ሐ) በንዑስ አንቀጽ 3 (ለ) ሥር የተጠቀሰው ውክልና በሥራ ላይ የሚቆየው የአካባቢው ብሔሮች እና ብሔረሰቦች ቁጥር አብላጫ እስኪሆን ወይም የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት እና ከዞን ወይም ከልዩ ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ብሔሮች እና ብሔረሰቦች ጋር በመመካከር ውክልናው እንዲቀር እስኪወስኑ ነው፡፡

c) The delegation mentioned under sub-article 3b is valid until the nations and nationalities of the locality become the majority or until the administrative council of the region and the council of zonal or especial woreda administration nations and nationalities discuss with to determine altering the delegation.

## 16. የከተማ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባራት

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 መሰረት ለከተማው የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተዉ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማው ምክር ቤት ከዚህ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፡፡

ሀ) በሕገ-መንግስቱ ለክልሉ ምክር ቤት የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በፌደራልና በክልል በወጡ ሕጐች እና እንደየአግባብነቱ በዞን ወይም በልዩ ወረዳ ወይም በወረዳ ባልተሸፈኑ ከተማ ነክ ጉዳዮች ላይ ደንብ ወይም መመሪያ ያወጣል፣

ለ) በዚህ አዋጅ ተለይተው በተሰጡ ጉዳዮች ላይ የገቢ ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን ይወስናል፣ መሰብሰቡን ያረጋግጣል፣ አስፈላጊ ማስተካከያ ያደርጋል፡፡

ሐ) የከተማው መሬት በሕግ መሠረት መተዳደሩን ያረጋግጣል፣

መ) የከተማውን ከንቲባ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ይሾማል፣

ሠ) በከንቲባው አቅራቢነት የከተማውን ምክትል ከንቲባና የከንቲባ ኮሚቴ አባላት ይሾማል፣

## 16. Powers and Duties of the Urban Center Council

1. Shall have powers and responsibilities to exercise power and duties given to the urban center on the basis of article 12 of this Proclamation.
2. Without prejudice to the general provision indicated on sub-article 1 of this article, the council of the urban center shall have the following powers and duties.

a. Without prejudice to the power vested on the council of the region by constitution, shall issue regulation or directive on the laws issued by federal and the region on the urban center connected matters in zone or especial woreda or woreda when appropriate.

b. Shall define the income collecting methods on the identified and given maters by this Proclamation; ensure if it is collected; retain necessary adjustment.

c. Ensure if the urban center land is administered on the basis of law.

d. Appoint mayor of the urban center from the members of the council.

e. Appoint deputy mayor of the urban center and committee members of the mayor based

ረ) አስፈላጊነታቸው የታመነባቸውን ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ያቋቁማል፣ የኮሚቴዎችን የሥራ ሁኔታ ይወስናል፣

ሰ) በዚህ አዋጅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የከተማውን አስተዳደር አደረጃጀትና አወቃቀር ያጸድቃል፣ ከንቲባው በሚያቀርበው ሃሣብ መሠረት የሥራ ኃላፊዎችን ሹመት ያጸድቃል፣

ሸ) የከተማ ነክ ጉዳዮች አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ኘሬዝዳንትና ዳኞች ይሾማል፣

ቀ)የከተማውን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት ያፀድቃል፣ በአግባቡ በሥራ መተርጎማቸውንም ያረጋግጣል፣

በ) ሥራ አመራሩ የሚመዘንበትን ዓመታዊ የሥራ አፈፃፀም መለኪያና ግቦች ያጸድቃል አፈፃፀምን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣

ተ) የተመሰከረለት የውጭ ኦዲተር ይሰይማል፣ ከኦዲተር በሚቀርበው ሪፖርት መነሻ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣

ቸ) ለአባላቱ እና ለከተማው ሌሎች ሠራተኞች የሥነ ምግባር ደንብ ያወጣል፣ ተፈፃሚነቱን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣

ነ) ምክር ቤቱ በሚቀርቡ ሪፖርቶች ላይ ተወያይቶ ያፀድቃል፣

ኘ) ለከተማው የተዘጋጁ የከተማ ፕላኖችን ያጸድቃል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣

አ) ከንቲባውንና የከንቲባ ኮሚቴ አባላትን አስፈላጊ ሲሆን ለጥያቄ ይጠራል፡

on the recommendation of the mayor.

f. Establish permanent or adhoc committees believed to be necessary; define the performance situation of the committees.

g. Ratify organization and structuring of the urban center administration on the basis of the power granted by this Proclamation; ratify the appointment of the duty leaders based on the mayor recommendation.

h. Appoint the president and the judges of the administrative court of the urban allied matters.

i. Ratify the annual job plan and budget of the urban center; ensure if they are implemented appropriately.

j. Approve the measurement and goals of the annual job performance to modernize the management; follow up and evaluate the implementation.

k. Assign authorized auditor, effect the relevant measure to be taken on the recommendation of the presented auditor report; follow up the implementation.

l. Issue the regulation of the ethics of the members and others employees of the urban center; follow up and ensure the implementation.

m. Ratify discussing on the report presented by the council.

n. Ratify the urban plans prepared to the urban center; follow up the implementation.

o. Subject mayor and the committee members of the mayor for enquiry when necessary.

## 17.የከተማው ምክር ቤት ተጠሪነትና የአሠራር ሥነ ሥርዓት

1. የከተማው ምክር ቤት ተጠሪነት ለመረጠው ሕዝብ ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና የሕጎችን አፈፃፀም፣ የገቢ አሰባሰብና የገንዘብ አጠቃቀምን በሚመለከት ተጠሪነቱ ለመረጠው ህዝብና ለክልሉ መንግስት ይሆናል፡፡
3. የምክር ቤቱ የስራ ዘመን አምስት ዓመት ሆኖ መደበኛና አስቸኳይ ጉባኤ ይኖረዋል፡፡ መደበኛ ጉባኤ በየሶስት ወሩ ይካሄዳል፡፡
4. በማናቸውም የምክር ቤቱ ስብሰባ ከጠቅላላ አባላቱ ከሁለት ሦስተኛ በላይ የሚሆኑት ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል፡፡
5. በማናቸውም የምክር ቤቱ ስብሰባ ውሳኔ ሊተላለፍ የሚችለው በስብሰባው ላይ ከተገኙት አባላት ከግማሽ በላይ ሲደግፉት ነው፡፡

## 18.ስለ ከተማ ምክር ቤት መበተን

የከተማው ምክር ቤት ሊበተን የሚችለው እንደ አግባብነቱ በክልሉ ሕገመንግስት አንቀጽ 62 በተመለከተው መሰረት ይሆናል፡፡

## 19.ጊዜያዊ የከተማ አማካሪ ምክር ቤት አወቃቀር

1. ማንኛውም ከተማ ወደ ፈርጅ ሶስት ደረጃ እንዲሸጋገር ሲወሰን በህዝብ ምርጫ የከተማ ምክር ቤት እስኪቋቋም ድረስ ለዞን፣ ለወረዳ፣ ለቀበሌ ከከተማው ከተመረጡት የምክር ቤት አባላት እንዲሁም በከተማው የተቋቋሙና

## 17. Accountability and working Principles of the Urban Center Council

1. The urban center council shall be accountable to the public.
2. Without prejudice to the provision on the sub-article 1 of this article, regarding policies, strategies and the laws implementation , the revenue collection and monetary custom shall be accountable to the people elect them and to the region government.
3. Terms of the council shall be five years and shall have regular and extraordinary meetings; the regular meetings shall be in three months interval.
4. In every meetings of the council, it shall be quorum of the meeting when more than two-third of the entire members are found.
5. In every meetings of the council, the decision shall be passed when supported by more than half of the members found in the meeting.

## 18. Dissolution of the Urban Center Council

The council of the urban center shall be suspended inaccordance with the relevant article 62 of the regional constitution.

## 19. Structuring the Provisional advisory Council of the Urban Center

1. When every urban center is decided to be transformed in to category three may effect to be directed by provisional council of the urban center whose members are the members of the council, elected from the urban center for zone, woreda,

የሥራ ባህርያቸው ከከተሞች ሥራ ጋር የበለጠ የሚያገናኛቸው ተቋማት የሥራ ኃላፊዎች እና የሕዝብ አደረጃጀቶች ተወካዮችና ታዋቂ ግለሰቦች አባል የሆኑበት ጊዜያዊ የከተማ ምክር ቤት እንዲመራ ሊደረግ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

2. አዲስ ወደ ፈርጅ ሶስት ደረጃ እንዲያድግ የተወሰነለት ከተማ ጊዜያዊ ከንቲባ በከተማው ጊዜያዊ ምክር ቤት ይሾማል፡፡
3. ጊዜያዊ የከተማ አማካሪ ምክር ቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 ንኡስ አንቀጽ 2 ከፊደል (ለ) እስከ ፊደል (ነ) የተደነገገውን ስልጣንና ተግባር ከመተግበር በስተቀር አዲስ ሕጎችን ማውጣት፣ ነባር ሕጎችን መሻር ወይም ማሻሻል አይችልም፡፡
4. በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ወደ ፈርጅ ሶስት የከተማ አስተዳደር ደረጃ እንዲሸጋገር የተወሰነለት ከተማ ጊዜያዊ የከተማ ከንቲባ ኮሚቴ ይኖረዋል፣
5. ጊዜያዊ የከተማ አስተዳደር ከንቲባ ኮሚቴ አባላት ሹመት በከንቲባው አቅራቢነት በከተማው ጊዜያዊ ምክር ቤት ይጸድቃል፡፡
6. በከተማው የተቋቋሙና የሥራ ባህርያቸው ከከተሞች ሥራ ጋር የበለጠ የሚያገናኛቸው ተቋማት የሥራ ኃላፊዎች የከተማ ከንቲባ ኮሚቴ አባላት ይሆናሉ፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡
7. የጊዜያዊ ከንቲባ ኮሚቴው ስልጣንና ተግባር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 4 ከፊደል (ለ) እስከ ፊደል (ቀ) የተመለከተው ይሆናል፡፡
8. የጊዜያዊ ከንቲባ ሥልጣንና ተግባር በሚመለከት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21 ንዑስ

kebele as well as the job leaders of the institutions that are established in the urban center and their job condition related to the urban center job, the public organization representatives and celebrity individuals until the council of the urban center is established by the public election , the detail shall be defined by regulation.

2. Temporary mayor for the urban center, that is newly determined to be grown to the category three grading, shall be assigned by the provisional council of the urban center.
3. Temporary advisory council of the urban center may not issue new laws, repeal or amend the existing laws except implementing powers and duties indicated in the sub-article 2 from letter (a) to letter(o) of the article 15 in this proclamation.
4. The urban center that is decided to be transformed to the category three urban center administration level by executive council of the region shall have temporary mayor committee of the urban center.
5. The appointment of the temporary mayor committee members of the urban center administration shall be ratified by the temporary council of the urban center based on the mayor recommendations.
6. The duty leaders of the institutions, that are established in the urban center and their job condition is more connected to the urban job, shall be the members of the urban center mayor committee. The detail shall be defined by regulation.
7. The powers and duties of the provisional mayor committee shall be indicated in sub-article 4 from letter (b) to letter (i) of article 21 of this proclamation.
8. Concerning powers and duties, the temporary mayor shall implement duties indicated in sub- article 1

አንቀጽ 1 ከ(ለ) እስከ (ኀ) እንዲሁም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 ንኡስ አንቀጽ 2 (ሀ)፣ከ(ሐ) እስከ (ፀ) እና ንኡስ አንቀጽ 3፣ 4 እና 5 የተመለከቱትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

9. በዚህ አዋጅ ለከንቲባ ኮሚቴ እና ለከንቲባ የተደነገገው ተጠሪነት እንደአግባብነቱ ለጊዜያዊ ከንቲባ ኮሚቴ እና ለጊዜያዊ ከንቲባው ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

10. የጊዜያዊ አማካሪ ምክር ቤት አፈጉባኤ፣ ምክትል አፈጉባኤ አሰያየም፣ተጠሪነት ሥልጣንናተግባር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 በተመለከተው አግባብ ይሆናል፡፡

## 20. የከተማ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ እና ምክትል አፈጉባኤ አሰያየም፣ ስልጣንና ተግባር

1. የምክር ቤቱ አፈጉባኤ እና ምክትል አፈጉባኤ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል የሚመረጥ ሆኖ ተጠሪነቱም ለምክር ቤቱ ይሆናል፡፡
2. የምክር ቤቱ አፈጉባኤ እና ምክትል አፈጉባኤ የሥራ ዘመን የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ይሆናል፡ ፡
3. የከተማ ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

ሀ) የምክር ቤቱን የመወያያ አጀንዳዎችን ያዘጋጃል፣ ስብሰባዎችን ይመራል፤

ለ) ምክር ቤቱ እንደአስፈላጊነቱ በቋሚና በጊዜያዊ ኮሚቴ የሚደራጅበትን ስልት ይነድፋል፣ ያቅዳል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

ሐ) በቋሚና በጊዜያዊ ኮሚቴ የሚቀርቡ ሪፖርቶችን ገምግሞ የውሳኔ ሃሳብ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣ ያስወስናል፣

መ) በአባላት ላይ የሚወሰደውን የዲሲፕሊን እርምጃዎች ያስፈጽማል፤

from (b) to (m) of article 21 in this Proclamation as well as sub-article 2(a) from (c) to (2e) and sub-article 3, 4 and 5 of article 12 in this Proclamation.

9. The provision for the mayor committee and mayor in this proclamation shall be implemented on the temporary mayor committee and the temporary mayor when appropriate.
10. The accountability, power and duty of the deputy spokesperson, who shall be appointed by the spokesperson of the adhoc advisory council, shall be the pertinent article 19 indicated in this proclamation.

## 20. Designation, Powers and Duties of the Spokesperson and Deputy Spokesperson of the Urban Center Council

1) The spokesperson and deputy spokesperson of the urban center council shall be elected from members of the council and accountable to the council.
2) Termsof the urban center spokesperson and the deputy spokesperson shall be the terms of the council.
3) The spokesperson of the urban center council shall have the following, powers and duties.
   a) Prepares the discussion agendas of the council and directs meetings;
   b) Designs and plans the system in which the council to be organized in permanent and adhoc committee when necessary; follows up the implementation;
   c) Presents the recommendation to the council by evaluating the reports presented by the permanent and temporary committee; effects to be determined.
   d) Effects the implementation of the disciplinary

ሠ) የምክር ቤቱን አባላት የአቅም ግንባታ ሥራ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ከሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ጋር በመቀናጀት ያስፈጽማል፤

ረ) የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በወቅቱ ለሚመለከታቸው ክፍሎች እንዲተላለፉ ያደርጋል፣ ተፈጻሚነታቸውን ይከታተላል፤

ሰ) ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ምክር ቤቱን ይወክላል፤

ሸ) በምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡

4. የከተማው ምክር ቤት ምክትል አፈጉባኤ ሥልጣንና ተግባራት፣

ሀ) ዋና አፈጉባኤ በሌለበት ተክቶት ይሰራል፡፡

ለ) በዋናው አፈጉባኤ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባር ያከናውናል፡፡

measures on the member.

e) Prepares the capacity building activity plan of the council members; effects to be implemented in collaboration with the concerned executive members.

f) Effects the council decisions to be passedtimely to the concerned divisions; follows up the implementation.

g) Represents the council in the relationships with the third party.

h) Performs others duties given by the council.

4. Power and duties of the deputy spokesperson of the urban center council;

a. Duty for in the absence of the chief spokesperson;

b. Implements others duties that are separately given by the council.

## 21. የከንቲባ አሰያየም፣ ተጠሪነትና የሥራ ዘመን

1. አሰያየም

ሀ) ከንቲባው ከምክር ቤቱ አባላት መካከል የሚመረጥ ሆኖ፣ በከንቲባው አቅራቢነት ሌሎች የከንቲባ ኮሚቴ አባላት ይሾማሉ፡፡

ለ) በከተማው ውስጥ የሚኖረው የአካባቢ ብሔረሰቦች ቁጥራቸው አብላጫ ባለመሆኑ ምክንያት የምክር ቤቱ የተወሰነ መቀመጫ ለብሔረሰቦቹ እንዲሆን የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚወሰንበት ጊዜ ከንቲባው ከከተማው ደረጃ ጋር ተመጣጣኝ ብቃትና ችሎታ ያለው ሆኖ የሚመረጠው ከአካባቢው ብሔረሰብ ምክር ቤት አባላት መካከል ይሆናል፡፡

ሐ) ከንቲባው ከተማውን ለመምራት የሚያስፈልገው የትምህርት ዝግጅት፣ የሥራ አመራር ብቃትና

## 21. Designation, Accountability and Terms of theMayor

1. Designation

a) The mayor shall be elected from the members of the council, and others mayor committee members shall be appointed by the recommendation of the mayor.

b) When the regional executive council decides some seats of the council to be for the nationalities because of the local nationalities numbers living in the urban center is not the majority; the mayor shall be elected from the members of the locality nationality council who have potential and skill that meet the urban center standard.

c) The mayor shall have educational competence necessary to direct the urban

ክህሎት እንዲሁም ህዝባዊ ወገንተኝነት፣ መልካም አመለካከትና ስነምግባር ያለው፣ ከብልሹ አሰራር አመለካከትና ተግባር የፀዳ ሊሆን ይገባል፡፡

2. **ተጠሪነት**

የከንቲባው ተጠሪነት ለከተማው ምክር ቤት እና ለርዕሠ መስተዳድር ወይም ለዋና አስተዳዳሪ ይሆናል፡፡

3. **የሥራ ዘመን**

የከንቲባ የሥራ ዘመን የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ይሆናል፡፡

## 22. የከንቲባው፣ የምክትል ከንቲባውና የከንቲባ ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር

**1. የከንቲባው ሥልጣንና ተግባር**

ሀ) ከንቲባው በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 12 የከተሞች ሥልጣንና ተግባራት ተብለው የተዘረዘሩ ሥራዎች በበላይነት ይመራል፡፡

ለ) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 (ሀ) እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማው አስተዳደር ዋና ሥራ አስፈፃሚእና የከተማ አስተዳደር ምክር ቤት ሰብሳቢ ሆኖ ያገለግላል፣

ሐ) ከተማ አቀፍ ሥራዎችን በሚመለከት አዳዲስ ሃሳቦችን እያመነጨ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፣

መ) የደህንነት፣ ሕግ ማስፈፀም እና የአስቸኳይ ጊዜ ጉዳዮችን ጭምር የመንግሥት ሥራዎችን በኃላፊነት ይመራል፣

ሠ) የከንቲባ ኮሚቴን ሹመት ለምክር ቤቱ በማቅረብያስፀድቃል፣ያቋቁማል፣ሥራ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣ ምክትል ከንቲባውንም ያሾማል፣

ረ) በሥራ አመራር፣ አፈፃፀም እና በሙያዊ ብቃት መሠረት የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ሥራ

center, the management potential and skill as well as public approach a good outlook and ethics, and shall be free from corruption outlook and practice.

## 2. Accountability

The accountability of the mayor shall be to the urban center council and to the chief executive or to the chief administrator.

## 3. Terms of the Office

Terms of the mayor shall be the terms of the council.

## 22. Powers and Duties of the Mayor, Deputy Mayor and the MayorCommittee

**1. Powers and Duties of the Mayor**

a) The mayor shall direct the activities, the powers and duties of the urban center, listed in article 12 of this Proclamation;

b) Without prejudice to the sub-article 1(a) of this article, the mayor serves being the chief executive of the urban center administration and chairperson of the urban center administration council;

c) Presents, initiating new ideas concerning the urban activates, to the council; ensures the implementation on its approval;

d) Directs principally the government activities including the security , implementing law and the emergency time issues;

e) Effects the appointment of the mayor committee to be ratified and established by presenting to the council; follow up the implementation; effects the deputy mayor to be appointed;

f) Effects recruiting the municipality service manager and the appointment to be ratified by presenting to the council based on management,

አስኪያጅ በመመልመል ለምክር ቤቱ አቅርቦ ሹመቱን ያስጸድቃል፣

ሰ) የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች መቅረባቸውን ያረጋግጣል፣ ሕዝቡም ተገቢውን አገልግሎት በተገቢው ሁኔታ ማግኘቱን ይከታተላል፣

ሸ) የከተማ ነክ አስተዳደር ጉዳዮች ፍርድ ቤት ዳኞች በምክር ቤቱ ያሾማል፤

ቀ) ከተማው ከሌሎች አካላት ጋር የሚያደርጋቸውን ግንኙነቶች በተመለከተ ከተማውንይወክላል፣ ውል ይዋዋላል፤

በ) የከተማውን ረቂቅ በጀት ያዘጋጃል፣ ያስጸድቃል፣ የጸደቀውን በጀት አፈፃፀም ይከታተላል፣

ተ) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር፣ የከተማው የሥራ ኘሮግራም፣ የበጀት፣ የፋይናንስ አፈፃፀም እና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ሪፖርት የሚቀርቡበትን የህዝብ መድረክ ያዘጋጃል፤

ቸ) እቅዶች የሚገመገሙበትን መመዘኛ ማኑዋል ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ኀ) በምክር ቤቱ የሚሰጡ ሌሎች መሠል ተግባራትን ያከናውናል::

2. **ምክትል ከንቲባ**

ምክትል ከንቲባው እንደ አስፈላጊነቱ እስከ ፈርጅ ሶስት ባሉት ከተሞች የሚኖር ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል::

ሀ) ከንቲባዉ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ከንቲባው ተክቶት ይሠራል፤

ለ) ምክትል ከንቲባው ተጠሪነቱ ለከተማው ከንቲባ ይሆናል፤

ሐ)ምክትል ከንቲባው አንድ የሥራ ዘርፍ ወይም ሴክተር ኃላፊ ሊሆን ይችላል፣

መ) ምክትል ከንቲባው በከንቲባዉ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

3. **የከንቲባ ኮሚቴ አሰያየም**

ሀ) የከንቲባ ኮሚቴ አባላትን ከምክር ቤት ወይም

performance, and professional efficiency.

g) Ensures if the services of municipality are supplied; follow up if the public obtain the relevant service in relevant manner.

h) Effects the judges of the urban touch administration matters court to be appointed by the council.

i) Represents the urban center and concludes contract concerning the relations the urban center makes with others bodies.

j) Prepares the urban center draft budget and causes to be ratified; follows up the implementation of the ratified budget.

k) Prepares the public forum that the report of the urban activity program, the budget, the finance implementation, and others related issues are presented by discussing with the relevant bodies.

l) Prepares the criterion manual in which the plan is evaluated; implements upon its approval.

m) Implements others similar activities that are given by the council.

2. **Deputy Mayor**

Deputy Mayor shall exist in urban centers up to category three when necessary and shall have the following powers and duties;

a) Duty for the mayor in his absence;
b) Shall be accountable to the urban center mayor;
c) May be the head of a division or a sector;
d) Shall implement others activities given by the mayor.

3. **Designation of the Mayor Committee**

a) The mayor committee members may be assignment from the council or out

ከምክር ቤት አባላት ውጪ መሰየም ይቻላል፣

ለ) የከንቲባ ኮሚቴ አባላት ከንቲባዉ በሚያቀርበዉ ዕጩዎች ዝርዝር መነሻነት በምክር ቤት ይወሰናል፡፡

ሐ) የከተማ የከንቲባ ኮሚቴ አባላት ብዛት የከተማውን ገቢ አቅም እና የሥራ ስፋት ግምት ዉስጥ በማስገባት የሚወሰን ይሆናል፣ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

4. የከንቲባ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባራት

ሀ) ለከተማው ምክር ቤት ለውሳኔ የሚቀርቡትን ከተማ አቀፍ ደንቦችና የውሳኔ ሀሳቦች በማመንጨት እና በመቀመር እንዲሁም በማስፈጸም ይሠራል፡፡

ለ) የከተማውን አመታዊ የሥራ እቅድና በጀት በማዘጋጀት እና አፈፃፀሙን በመከታተል ከንቲባውን ይደግፋል፡፡

ሐ) በከተማ አስተዳደር ውስጥ የሚካሄደውን የመረጃ ልውውጥ እና የሥራ ግንኙነት እንዲጠናከር ድጋፍ ይሰጣል፣ ይከታተላል፡

መ) በጋራ ሊፈቱ የሚገባቸውን የሥራ አመራር ችግሮች በመመርመር እና በመፍታትእንዲሁም የሥራ አፈፃፀምን በመገምገም ረገድ ይሳተፋል፣

ሠ) በከተማው መልካም ልማታዊ አስተዳደርን ከማስፈን አንፃር የነዋሪውን ሕዝብ ችግሮች ይለያል፣ ምላሽ እንዲያገኙ ያደርጋል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣

of the council members;

b) The mayor committee members shall be determinedby the council based on the candidates list that the mayor presents as initiation.

c) The number of the urban center mayor committee members shall be determined by considering the potential of the urban center income and the magnitude of the activity; the detail shall be defined by regulation.

**4. Powers and Duties of the Mayor Committee**

a) Effect the urban regulations and decision ideas that to be presented for decision to the urban center council by initiation and analyzing as well as implementing.

b) Support the mayor by preparing and follow up the implementation of the annual job plan and budget of the urban center.

c) Follow up and provide support to reinforce the exchange of information and the job relation act upon in the urban administration.

d) Participate in the aspect of examining and solving management problems to be solved mutually as well as evaluating the job performance.

e) Identify the problem of the resident public in order to settle a good developmental administration in the urban center; effect to obtain response;

ረ) ለነዋሪው ሕዝብ ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች በአግባቡ መቅረባቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ እንዲቀርብም ያደርጋል፣

ሰ) የመንግስትን ፖሊሲ ከማስፈፀምና የነዋሪውን ሕብረተሰብ ፍላጎት ከማሟላት አንፃር የከተማውን የማስፈጸም አቅም ማጠናከር ስለሚቻልበት ሁኔታ አዳዲስ ሀሳቦችን ያመነጫል፣ ጥናት እንዲካሄድ ያደርጋል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

ሸ) እያንዳንዱ የከንቲባ ኮሚቴ አባል በአንድ ወይም ከዚያ በበለጠ የሥራ ዘርፍ የሥራ አስፈጻሚነት ሚና ሊኖረው ይችላል።

ቀ) በማዘጋጃ ቤት ስር ያሉ ተቋማት የሥራ ኃላፊዎች ብቃት በማረጋገጥ ምደባ ይሰጣል፣

በ) የከንቲባ ኮሚቴዉ የሥራ ዘመን የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ይሆናል።

## 23. የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች እና የከተማው ሴክተር መስሪያ ቤቶች ጽህፈት ቤት

የመምሪያዎች፣የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች ጽህፈት ቤት፣ የጽህፈት ቤቶች እና የሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ኃላፊዎች ተጠሪነታቸው ለከንቲባ እና ለከንቲባ ኮሚቴ ይሆናል፤ ሥልጣንና ኃላፊነታቸው በደንብ ይወሰናል።

## 24. የማዘጋጃ ቤት ሥራአስኪያጅ ሥልጣንና ተግባራት፣

1. የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለከንቲባው እና በቴክኒክ ጉዳዮች ለሚመለከተው ቢሮ ሆኖ የሚከተሉት

follow up the implementation.

f) Follow up and supervise if the municipality services provided appropriately to the resident public; effect to be provided.

g) Initiate new ideas on the condition to strengthen the potential of the urban implementation in order to implement the government policy and fulfill the need of the resident society; effect the study to be conducted; follow up and support the implementation upon its approval.

h) Each member of the mayor committee may have executive role in one or more careers stream.

i) Provide assignment by approving the efficiency of the leader in the institutions under the municipality.

j) Terms of the mayor committee shall be the terms of the council.

## 23. Office of the Municipality Services and the Urban Sector Organization

The accountabilities of sector organizations , office of the municipality services, the offices and others service provider organizations leaders shall be to the mayor and the mayor committee; their power and responsibility's shall be defined by regulation.

## 24. Power and Duties of the Municipality Manager

1) The manager of the municipality service shall be accountable to the mayor and to the concerned bureau in technical issues and shall have the following responsibilities and duties;

ኃላፊነትና ተግባራት ይኖሩታል፣

ሀ) የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶችን ሥራ ያቅዳል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል፤

ለ) የአገልግሎት አቅርቦት ደረጃዎችን፣ የአፈጻጸም መመዘኛዎችን እያዘጋጀ ለከንቲባው ሀሳብ ያቀርባል፤ በምክር ቤቱ ሲጸድቅ በአግባቡ በሥራላይ መዋሉን ያረጋግጣል፡፡

ሐ) ከማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች ጋር የሚዛመዱ የምክር ቤት ዉሳኔዎች መተግበራቸውን፣ እንዲሁም የመንግሥት ፖሊሲዎች እና ሕጎች መፈፀማቸውን፣ ደረጃዎች መጠበቃቸዉን እና በተግባር መተርጎማቸውን ያረጋግጣል፡፡

መ) የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች ኃላፊዎችን ወይም የሥራ መሪዎችን የሚያካትት የሥራ አመራር ቡድን ያቋቁማል፤ይመራል፤ቡድኑም የሥራ ቅንጅት፤ የመረጃ ልውውጥ የተባበረ የሥራ መንፈስ፤ የሥራ ውጤታማነት፤ እንዲኖር ይገመግማል፣ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

ሠ) ምክትል ሥራ አስኪያጆችን ለከንቲባ ኮሚቴ አቀርቦ እንዲሾሙ ያደርጋል፣ የሥራ ክፍል አስተባባሪዎችን ያስመድባል፣

ረ) የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች ሠራተኞችን በህጉና በደንቡ መሰረት ይቀጥራል፣ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅሞቻቸዉን ይወስናል፣ያሳድጋል፣ ይመራል፣ ከሥራ ማሰናበትን የሚያካትት የሥነ ሥርዓት እርምጃ ይወስዳል፣

ሰ) በማዘጋጃ ቤት መቋቋም ስለሚገባቸዉ ስለአዳዲስና የተሻሻሉ የተለያዩ አገልግሎት ሠጪ የሥራ ክፍሎች እና ጽህፈት ቤቶች አደረጃጀትና አወቃቀር ለከንቲባዉ ሀሳብ ያቀርባል፣ በምክር ቤት ሲጸድቅም በተግባር ላይ ያውላል፤

ሸ) የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች ዓመታዊ የሥራ እቅድ እና የበጀት ዝግጅትን ሂደትይመራል፣

a) Plans, directs and coordinates the activities of the municipality services.

b) Provides initiative idea to the mayor by preparing the standards of the service supply performance criteria, ensures if it is exercised properly when ratified by the council.

c) Ensures if the decisions of the council related with the municipality services are implemented; the government policies and laws are implemented; the standards are kept an practically applied.

d) Establishes and directs the management group which includes the heads of the municipality services or the duty leaders; evaluates the group to have the job integrity, exchanging information, cooperative spirit of the job and the job effectiveness; provides follow up and support.

e) Effects deputy managers to be appointed by presenting to the mayor committee, effects the work division coordinators to be assigned.

f) Employs workers of the municipality services on the basis of the law and the regulation; determines their salary and benefit; upgrade, direct; effects the ethical measures which include suspending from a job.

g) Presents initiative idea to the mayor on the new and improved diverse service provider work division and organizing and structuring of offices to be established in the municipality; implements when ratified by the council.

h) Directs the annual job plan and the budget preparation process of the mutuality services; presents the prepared draft to the mayor;

የተዘጋጀውን ረቂቅ ለከንቲባዉ ያቀርባል፣ ምክር ቤቱ ሲያጸድቀውም ይተገብረዋል፣ ወቅታዊ የስራ ሪፖርቶች ለከንትባዉ ያቀርባል፤

ቀ) በምክር ቤቱ ስብሰባዎች ላይ በመገኘት የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች ስላሉበት ሁኔታ ማብራሪያና ምላሽ ይሰጣል፡፡

በ) ከከንቲባዉ ጋር በመወያየት የከተማዉን ገቢ ለማሻሻል የሚረዱ እርምጃዎች ይወስዳል፣ በከተማውና በነዋሪዉ መልካም አኗኗር ላይ ተጽዕኖ ባላቸዉ ነገሮች ሁሉ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ለከንቲባዉና ለምክር ቤቱ መረጃና ሃሳብ ያቀርባል፣

2. ከንቲባ ባለባቸው ከተሞች ለማዘጋጃ ቤት ሥራ አስኪያጅ የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ከንቲባ በሌላቸው ከተሞች ማዘጋጃ ቤት ሥራ አስኪያጅም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## የከተሞች ውስጣዊ አደረጃጀት

### 25.የክፍለ ከተማ አደረጃጀትና አወቃቀር

1. የክፍለ ከተማ አደረጃጀት በሬጂዮፖሊስ ከተማ ብቻ የሚደራጅ ይሆናል፡፡
2. የክፍለ ከተማ አደረጃጀትና የሚኖሩት አካላት፣ ኃላፊነትና ተግባራት በደንብ ይወሰናል፡፡

### 26.የከተማ ቀበሌ የመንግስት ሥልጣን አካላት

የከተማ ቀበሌ የመንግስት አስተዳደር መዋቅር ሆኖ የሚከተሉት የሥልጣን አካላት ይኖሩታል፣

1. የከተማ ቀበሌ ምክር ቤት፣
2. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት፣
3. ማህበራዊ ፍርድ ቤት፣

### 27.የከተማ ቀበሌ ምክር ቤት

1. በከተሞች የቀበሌ ነዋሪ ሕዝብ ከፍተኛው የሥልጣን አካልነው::
2. የከተማ ቀበሌ ምክር ቤት አባላት በቀጥታ

implements when ratified by the council; presents current job reports to the mayor.

i) Provides explanation and response on the condition that the municipality services are by attending on the council meetings.

j) Effects measures help to improve the urban center income by discussing with the mayor; provides information and idea to the urban center and the council decision to be given on all effects that have positive impact on the urban center and resident living.

2) Powers and duties given to the municipality manager in the urban center having mayor shall be applicable on the municipality managers in the urban center have no mayor.

## CHAPTER FIVE

## Internal Organization of the Urban Center

### 25. Organization and Structure of the Sub-City

1. Only city of ragiopolis shall have the sub-city organization.
2. Organization and its bodies, responsibilities and duties of the sub-city shall be defined by regulation,

### 26. The Government Power Organs of the Urban Center Kebele

The urban center kebele shall be the structure of government administration and shall have the following power organs;

1. Council of the urban center kebele;
2. Council of the kebele administration ;
3. Social court

### 27. Council of the Urban Center Kebele

1. The resident public of the urban center kebele is the higher power body.

በከተማ ቀበሌ ነዋሪ ሕዝብ የሚመረጡ ይሆናል። ተጠሪነታቸውም ለመረጠው ሕዝብ ነው።

**28. የከተማ ቀበሌ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር**

የከተማ ቀበሌ ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1. ከመንግስት ፖሊሲዎችና ሕጎች ጋር በማይቃረን መልኩ በአካባቢው ጉዳዮች ላይ የአፈፃጸም መመሪያዎችን ያወጣል፣
2. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል የከተማ ቀበሌ ዋና አስተዳዳሪን በምርጫ ይሰይማል፣ የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባላትን ሹመት ያጸድቃል፣
3. የመንግስት ፖሊሲዎችንና ሕጎችን፣ በከተማው ቀበሌ ለመተግበር የሚያስችል መርሃግብር ያዘጋጃል፣ አፈፃጸሙንም ይከታተላል፣
4. የከተማው ቀበሌ ነዋሪ ሕዝብ በቀበሌው ልማትና በመልካም አስተዳደር ጉዳዮች ላይበንቃት እንዲሳተፍ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣
5. የከተማው ቀበሌ ነዋሪ ሕዝብ ሰላምና ደህንነትመጠበቁንና ሕግና ሥርዓት መከበሩንያረጋግጣል፣
6. የቀበሌውን ዋና አስተዳዳሪና ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች ለጥያቄ ይጠራል፣ አሰራራቸውንም ይገመግማል፣
7. በከተማ ቀበሌ አስተዳዳሪ የሚቀርቡ ዓመታዊና ወቅታዊ ሪፖርቶችን መርምሮ ውሳኔይሰጣል፣

2. The members of the urban center kebele council shall be elected directly by the resident public of the urban center kebele. Their accountability shall be to the public that elect them.

**28. Powers and Duties of the Urban Center Kebele Council.**

The urban center kebele council shall have the following powers;

1. Issue the implementation directives on the locality affairs which do not oppose polices and laws of the government.
2. Assign a chief administrator of the urban center kebele from the members of the councilby election; ratify the appointment of the members of kebele administration council;
3. Prepare the schedule to implement the policies and laws of the government in the urban center kebele; follow up the implementation.
4. Facilitate the condition in which the urban center keele resident people actively participate on development and good governance affairs of the kebele,
5. Ensure if peace and security of the urban center kebele resident people are kept and laws and ethics are respected.
6. Subject the chief administrator of the kebele and others duty leaders for inquiry, evaluate their duty procedure,
7. Provide decision by examining the annual and current reports to be presented by the

8. ለቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ የሚጠቅሙ ሌሎች ተጨማሪ እቅዶችን ያዘጋጃል፣ ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል።

## 29. የከተማ ቀበሌ ምክር ቤት አፈጉባኤ እና ምክትል አፈጉባኤ

1. የከተማ ቀበሌ ምክር ቤት ከምክር ቤቱ አባላት መካከል በሚመረጡ አፈጉባኤና ምክትል አፈጉባኤ ይመራል።
2. በዚህ አዋጅ ስለ ከተማ ምክር ቤት አፈጉባኤ እና ምክትል አፈጉባኤ ስልጣንና ተግባር አስመልክቶ የተደነገጉት ለከተማ ቀበሌ ምክር ቤት አፈጉባኤ እና ምክትል አፈጉባኤ እንደአግባብነቱ ተፈፃሚ ይሆናል።

## 30.የከተማ ቀበሌ ምክር ቤት የስብሰባ ጊዜና የሥራ ዘመን

1. የከተማ ቀበሌ ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባውን በወር አንድ ጊዜ ያካሂዳል።
2. ከምክር ቤቱ አባላት ከሁለት ሶስተኛ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል። የምክር ቤቱ ውሳኔ በጉባኤው ላይ በተገኙ የምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምጽ ይተላለፋል።
3. የከተማ ቀበሌ ምክር ቤት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል። የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ከማብቃቱ አንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል። የቀድሞው ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ 15 ቀናት ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል።
4. ምክር ቤቱ መደበኛ ጉባኤ በማያደርግበት

urban center kebele administrator.

8. Prepare others additional plans that are useful to the kebele resident people; follow up their implementation.

## 29. Spokesperson and Deputy Spokesperson of the Urban Kebele Council

1. The urban kebele council shall be directed by spokesperson and deputy spokesperson who are elected from the members of the council.
2. In this Proclamation, the provision concerning to the powers and duties of the spokesperson and deputy spokesperson of the urban center council shall be applicable on the spokesperson and deputy spokesperson of the urban kebele council when appropriate.

## 30. Meeting and Terms of the Urban Kebele Council

1. The urban kebele council shall conduct regular meeting once in a month.
2. It shall be quorum when more than two third of the council members found. The decision of the council shall be passed by the majority vote of the council members found in the meeting.
3. Terms of the urban kebele council shall be five years; competed by conducting a new election ahead the end of terms of the council; a new council shall start the work within 15 daysfrom the completion date of the terms of the former council.
4. The spokesperson may call for emergency

ወቅት አፈጉባኤው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል አንድ ሶስተኛ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈጉባኤው ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት፡፡

**31. የከተማ ቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት**

የከተማ ቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት የቀበሌውን ዋና አስተዳዳሪ ጨምሮ በቀበሌ ውስጥ የሚገኙ መንግስታዊ ተቋማት ኃላፊዎች በአባልነት የሚገኙበት አካል ነው፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

**32.የከተማ ቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር**

የከተማ ቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. የከተማ ቀበሌ ምክር ቤት ያጸደቃቸውን የልማት ዕቅዶችና ፕሮግራሞች በሥራ ላይ ያውላል፣ የራሱን የልማት ዕቅዶችን ይነድፋል፣ በከተማው ምክር ቤት ያስጸድቃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣
2. በከተማ ቀበሌው ውስጥ በሕብረተሰብ ተሳትፎ የሚከናወኑ የልማት ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ሕዝቡንም ለልማት ሥራ ያነሳሳል፣
3. የከተማ ቀበሌ ሰላምና ፀጥታ ያስከብራል፣ ሕገ-ወጥ የመሬት ወረራንና የፕላን ጥሰትን ይከላከላል፣የመሰረተልማት፣ የኢንተርፕራይዞች፣ የቤት እና አረንጓዴ ልማት፣ የአካባቢ ጽዳትና ውበት፣ ሥራዎችን አፈፃፀም ይከታተላል፣
4. ከከተማው ቀበሌ ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**33.የከተማ ቀበሌ ዋና አስተዳደሪ አሰያየምና የሥራ ዘመን**

meeting in the time that the council does not conduct a regular meeting. The spokesperson shall be obliged to call for meeting when one third of the council members request for emergency meeting.

**31. Council of the Urban Kebele Administration**

The urban kebele administration council is a body in which the heads of governmental institutions found in the kebele, including the chief administrator of the kebele, are establish as members. The details shall be defined by regulation.

**32. Powers and Duties of the Urban Kebele Administration Council**

The urban kebele administration council shall have powers and duties indicated below:

1. Implement the development plans and programs that the urban kebele council ratify; draft its development plan; effect to be ratified by the urban council and implement.
2. Coordinate developmental activities performed by the participation of the society in the urban center kebele; encourage the public for the development activity.
3. Effect the peace and security of the urban center kebele to be respected; prevent illegal land invasion and plan violation; follow up the implementation of infrastructure, enterprises, the house and green development, environmental sanitation and attractiveness activities.
4. Implement others duties provided by the urban kebele council.

**33. Designation and Terms of the Urban Kebele Chief Administrator**

1. የከተማ ቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ ከከተማው ቀበሌ ምክር ቤት አብላጫ ድምጽ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች አቅራቢነት በምርጫ ይሰየማል፡፡
2. የከተማው ቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፡፡

**34.የከተማ ቀበሌ ዋና አስተዳደሪ ሥልጣንና ተግባራት**

የከተማ ቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ ተጠሪነቱ ለከተማ ቀበሌው ምክር ቤት ሆኖ የቀበሌው አስተዳዳሪና የሥራ መሪ ነው፡፡ የቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. በከተማው የቀበሌ ምክር ቤት የሚወሰኑ ተግባራትንና የውስጥ አደረጃጀት ያስፈጽማል፣ ይመራል፣
2. መንግስት የበላይ አካላት የሚወጡትን ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና እቅዶች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡
3. ለከተማው ቀበሌ ምክር ቤት ለነዋሪው ሕዝብ እና አግባብነት ላላቸው አካላት በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል፡፡
4. የከተማውን ቀበሌ ዓመታዊ ዕቅድ እና በጀት በማዘጋጀት ለምክር ቤት ያቀርባል፣ ያስጸደቃል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡
5. የህብረተሰቡን የልማት ተሳትፎ ያስተባብራል፣ የተለያዩ ኮሚቴዎች እንዲቋቋሙ ያደርጋል፣
6. ከከተማ ቀበሌ ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፣

**35.የከተማው ቀበሌ ምክትል ዋና አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባራት**

1. The urban kebele chief administrator shall be assigned from political organization that obtained the majority vote from the urban kebele council or by election on the proposal of the political organizations.
2. Terms of the urban kebele chief administrator shall be five years.

**34. Powers and Duties of the Urban Kebele Chief Administrator**

The urban kebele chief administrator shall be accountable to the urban kebele council and shall be the kebele administrator and duty leader; shall have powers and duties indicated below;

1. Effects the implementation and directs duties and internal organization to be decided by urban kebele council.
2. Follows up and supervises if policies, laws, regulations, directives and plans that are issued by superior government bodies are implemented.
3. Presents report regularly to the urban kebele council, resident people and appropriate bodies.
4. Presents the annual plan and budget of the urban kebele to the council by preparing; effects to be ratified; follows up the implementation.
5. Coordinates the development participation of the society; effects different committees to be established.
6. Implements others activities that are given from urban kebele council.

**35. Powers and Duties of the Urban Kebele Deputy Chief Administrator**

ምክትል ዋና አስተዳዳሪው ተጠሪነቱ ለዋና አስተዳዳሪ እና ለከተማ ቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ሆኖ፣

1. ዋና አስተዳዳሪ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶት ይሰራል፣
2. በከተማ ቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት እና በቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ ተለይተው የተሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## 36.የከተማ ቀበሌ አስተዳዳሪ ጽህፈት ቤት

1. የከተማ ቀበሌውን ጽህፈት ቤት በበላይነት የሚመራው የከተማው ቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ ይሆናል።
2. የከተማ ቀበሌ ጽህፈት ቤት አደረጃጀት፣ሥልጣንና ተግባር በደንብ ይወሰናል።

## 37. የከተማ ቀበሌ መንግስታዊ ተቋማት አደረጃጀትና አወቃቀር

የከተማ ቀበሌ የተለያዩ መንግስታዊ ተቋማት አደረጃጀትና አወቃቀር ይኖሩታል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

## 38.የከተማ ቀበሌ ጊዜያዊ ምክር ቤት

1. በምርጫ ቦርድ ሕግ መሰረት በከተሞች ምክር ቤት ምርጫዎች መካከል አዲስ የከተማ ቀበሌያት አደረጃጀት ለውጥ ሲደረግ ጊዜያዊ የቀበሌ ምክር ቤት ሊደራጅ ይችላል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።
2. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 27 ከንዑስ አንቀጽ 2 እስከ ንዑስ አንቀጽ 8 የተመለከተው የከተማ ቀበሌ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር የጊዜያዊው ቀበሌ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር ይሆናል።

Deputy Chief administrator shall be accountable to the chief administrator and to the urban kebele administration council; and

1. Duty for in the absence of chief administrator;
2. Implements others duties separately given by the urban kebele administration council and by kebele chief administrator.

## 36. Office of the Urban Kebele Administrator

1. The urban kebele office shall be directed principally by the urban kebele chief administrator.
2. The organization, powers and duties of the urban kebele office shall be defined by regulation.

## 37. Organization and Structure of the Urban kebele Governmental Institutions

The urban kebele governmental institutionsshall have different organization and structure. The details shall be defined by regulation.

## 38. Temporary Council of the Urban Kebele

1) According to the electoral board's law, when change is made in the new urban kebele organization by urban center council's election, the temporary kebele council may be organized; the details shall be defined by regulation.
2) The powers and duties of the urban kebele council indicated in sub-article 2 to sub-article 8 of article 27 in this Proclamation shall be the powers and duties of temporary kebele council

## ምዕራፍ ስድስት

## ስለከተማ ቀጠና

### 39. የከተማ ቀጠና አደረጃጀት

በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 መሰረት የከተማ ቀጠና የሚደራጅ ሆኖ ከዚህ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡፡

ሀ) የሕዝብ መማክርት ምክር ቤት፣

ለ) ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣

ሐ) ማህበራዊ ፍርድ ቤት እንደአስፈላጊነቱ፣

### 40. በከተማ ቀጠና የሕዝብ መማክርት ምክር ቤት አደረጃጀት

1. በከተማ ቀጠና የሕዝብ መማክርት ምክር ቤት ይደራጃል፡፡ የመማክርት ምክር ቤቱ አባላት ውክልና እና የምክር ቤቱ አመሰራረት በደንብ ይወሰናል፡፡
2. የቀጠና እና የሰፈር የሕዝብ መማክርት ምክር ቤት በደረጃው ከሚገኙ የሕዝብ የልማትአደረጃጀቶች በሚወከሉ ተወካዮች የሚመሰረት ይሆናል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

### 41.የቀጠና መማክርት ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባራት

የቀጠና መማክርት ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. በቀጠናው የመንግስት ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች እንዲተገበሩ ያደርጋል፣ አፈፃማቸውን ይከታተላል፡፡
2. የቀጠናው ነዋሪዎች ልማታዊ ተሳትፎ እንዲጎለብት ያደርጋል፣ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

## CHAPTER SIX

## Urban zone

### 39. Organization of the urban zone

Sub-City shall be organized on the basis of sub article 2 and 3 of article 5 in this proclamation and shall have the following organs.

a) Public advisory Council,
b) Executive committee,
c) Social court when necessary.

### 40. Organization of the Public Analyst Council in the Sub-City

1. The public analyst council shall be organized in sub-city. Delegation of advisory council shall be defined by regulation.
2. The sub-city and locality public analyst council shall be established by the representative to be delegated from public development organization found in each level. The details shall be defined by regulation.

### 41. Powers and Duties of the Sub-City Advisory Council

The sub-city advisory council shall have the powers and duties indicated below:

1. Effect the government policies, laws, regulations and directives to be implemented in the sub-city; follow up the implementation.
2. Effect developmental participation of the sub-city residents to be increased. The details shall be defined by regulation.

## 42.የቀጠና የሕዝብ መማክርት ምክር ቤት ተጠሪነት

የቀጠና የሕዝብ መማክርት ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለቀጠናው ነዋሪ ህዝብ እና ለከተማው ቀበሌ አስተዳደር ይሆናል፡፡

## 43.የቀጠና ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ

1. የከተማ ቀጠናው ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በቀጠናው የሚገኙ መንግስታዊ ተቋማት የሥራ ኃላፊዎች አባል ሆነው የሚደራጅ አካል ሲሆን ከመካከላቸው ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ፀሐፊ ይመረጣል፡፡ የኮሚቴው ኃላፊነትና ተግባር በደንብ ይወሰናል፡፡
2. የቀጠና ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተጠሪነት ለቀጠናው የሕዝብ መማክርት ምክር ቤት እና ለከተማ ቀበሌው አስተዳደር ምክር ቤት ይሆናል፡፡

### ምዕራፍ ሰባት
### ስለፍርድ ቤቶች እና የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው ሌሎች አካላት

## 44.መደበኛ ፍርድ ቤቶች

1. እስከ ፈርጅ ሶስት ድረስ ላሉ ከተሞች መደበኛ ፍርድ ቤቶች ይኖሯቸዋል፡፡
2. የከተማመደበኛ ፍርድ ቤቶች አደረጃጀት አሠራር ሥልጣንና ተግባር እንዲሁም የዳኞች አሰያየም በክልሉ የፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ መሠረትና በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በኩል ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 45.የከተማ ነክ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት አደረጃጀት

1. ማንኛውም ከተማ እንደ ገቢ አቅሙና እንዳሉት ጉዳዮች ብዛት በተናጥል ወይንም

## 42. The Accountability of the Sub-City Public Analyst Council

Public analyst council of the sub-city shall be accountable to the sub-city residential people and to the urban kebel administration.

## 43. Executive Committee of the Sub-City

1. Executive committee of the sub-city shall be a body organized from the member of governmental institutions duty leaders found in the sub-city; and chairperson, deputy chairperson and secretary are elected from them. The responsibility and duties of the committee shall be defined by regulation.
2. Executive committee of a sub-city shall be accountable to the public analystcouncil of the sub-city and to the urban kebele administration Council.

### CHAPTER SEVEN
### Courts and Others Organs Granted with Judiciary Power

## 44. Regular Courts

1. Urban centers up to category three shall have regular courts
2. Organization procedure, powers and duties as well as judges appointment of the urban center regular court shall be applicable on the basis of regional court establishment Proclamation and by the judge's administration commission of the region.

## 45. Organization of the Urban Allied Administrative Court

ከአጎራባች ከተሞች ጋር በመቀናጀት የከተማ ነክ ጉዳዮች አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ሊያቋቁም ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

2. የከተማ ነክ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ ከዚህ የሚከተሉት ሁለት እርከኖች ይኖሩታል፣

ሀ/ የመጀመሪያ ደረጃ የከተማ ነክ አስተዳደደራዊ ፍርድ ቤት እና

ለ/ የይግባኝ ሰሚ ከተማ ነክ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት፣

1. Every urban center may establish urban allied issues administrative court individually or by integrating with the neighbor urban center according to revenue, potential and number of issues they have. The details shall be defined by regulation.
2. The urban allied administrative curt shall have the following two occasion.

a) The urban allied administrative court of the first instance.

b) The urban allied administrative court of the appeal hearing.

## 46.የከተማ ነክ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የከተማ ነክ ጉዳዮች አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ከሚከተሉት ጉዳዮች በሚመነጩ ክርክሮች ሥልጣን ይኖረዋል፣

ሀ) የከተማ መሬት አጠቃቀም ፕላን አተገባበር፣

ለ) የከተማ ቦታ አጠቃቀም፣

ሐ) የህገ ወጥ ይዞታና ግንባታ፣

መ) በመሰረተ ልማት ላይ የሚፈጸሙ ጉዳቶችን፣

ሠ) የሥራ ፈቃድና እድሳት፤

ረ) የአካባቢ ፅዳት እና የድምጽ ብክለት፣

ሰ) በነዋሪዎች ጤና እና ንብረት ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ በሚችሉ ጉዳዮች፣

ሸ) የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች፣

ቀ) በከተሞች ሕንፃ ግንባታ ህጎች ጥሰት፣

ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

## 46. Powers and Duties of the Urban Allied Administrative Court

1. The urban allied administrative court shall have powers on disputed initiative from the following issues:

a) Implementation of the urban land utilization plan,

b) The ulilization of the urban land.

c) Illegal ownership and construction;

d) Disstructions implemented on infrasstratctaure

e) Job licence and renewal,

f) Environmental sanitation and sound pollution,

g) Issues may cause harm on the health and property of the residents;

h) Services of the manuciqality;

i) Prejudise to the laws of the construction of urban building. The details shall be defined by regulation.

2. የመጀመሪያ ደረጃ የከተማ ነክ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተዘረዘሩት ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን ይኖረዋል፡፡
3. የይግባኝ ሰሚው የከተማ ነክ ጉዳዮች አስተዳደር ፍርድ ቤት ከመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በይግባኝ የሚቀርቡ ጉዳዮችን አይቶ የመወሰን ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ ውሳኔውም በፍሬ ነገር ጉዳዮች ላይ የመጨረሻ ይሆናል፡፡
4.የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የህግ ስህተትን በተመለከተ የሚቀርቡ የይግባኝ ጉዳዮች የማየት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
5.የከተማ ነክ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ የሚሰጠው አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ሆኖ መደበኛ የሥነ-ስርዓት ህጎችን ለመከተል አይገደድም፡፡

## 47.ማህበራዊ ፍርድ ቤት

1. የማህበራዊ ፍርድ ቤት ተጠሪነቱ ለቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ይሆናል፡፡
2. ስለማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች አሿሿም ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡
3. የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የማህበራዊ ፍርድ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ በከተማ ቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ምዕራፍ ስምንት

## ለከተሞች የሚደረግ ድጋፍ

## 48. ለከተሞች የሚደረገው ድጋፍ

1. የክልሉ መንግስት ለከተሞች የሚያደርገው

2. The urban allied administrative court of the first instance shall have the first level of power on the issues listed on the sub-article 1 of this article.
3. The urban allied administrative court of the appeal hearing shall have the power to examine and decide on issues presented as appeal from first instance court. The decision on the core issues shall be the end.
4. The supreme court of the region shall have the power to examine the appealing issues presented concerning the law error.
5. The urban allied administrative court shall provide decision on the basis of the pertinent law and shall not be obliged to follow up the laws of the regular procedure.

## 47. Social court

1. The social court shall be accountable to the kebele administration council;
2. The appointment of social court judges shall be defined by regulation.
3. Without prejudice to the provisions on this Proclamation, the Proclamation of the social court establishment shall be implemented on the urban center Kebele social court.

## CHAPTER EIGHT

## Support for the Urban Centers

## 48. Support for the Urban Centers

ፕሮጀክት ተኮር ድጋፍ እንደተጠበቀ ሆኖ አቅም በፈቀደ መጠን ፍትሐዊ በሆነና በከተሞች ተወዳዳሪነት ላይ የተመሰረተ የልማት ድጋፍ ያደርግላቸዋል፣ እንዲሁም ፈጥነው የሚለሙበትንና የሚያድጉበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

2. የዞኖች፣ የልዩ ወረዳ እና የወረዳ አስተዳደሮች በስራቸው የሚገኙትን ሁሉንም ከተሞች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው አግባብ የበጀት እና ሌሎችንም ድጋፎች በመስጠት ማቋቋም እና ልማታቸውን ለማፋጠን የሚያስችል ሁሉን አቀፍ ድጋፍ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የዞኖች፣ ልዩ ወረዳዎችና የወረዳ አስተዳደሮች በስሮቻቸው የሚገኙትንናወደ ከተማነት አዲስ የሚሸጋገሩትን ከተሞች በበጀት፣ በሰው ኃይል እና በማቴሪያል በመደገፍ ማቋቋም ይኖርባቸዋል፡፡

## 49.ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ

እያንዳንዱ ከተማ ወቅታዊ የልማት እቅድ አፈፃፀም፣ የበጀት አጠቃቀም እና የኦዲት ሪፖርቶች በየደረጃው ለሚገኙ አግባብ ላላቸው የመንግሥት አካላትየማቅረብ ግዴታ አለበት፤

## 50.የከተሞች ነፃነት

ማንኛውም ከተማ ሕገመንግስቱንና ሕገመንግስታዊ ሥርዓቱን በጠበቀ አግባብ በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በነፃነት የማከናወን መብት አለው፡፡

## 51.የሕዝብ ተሳትፎን ስለማረጋገጥ

1. የከተማዉ ነዋሪዎች፣ ሲቪክ ማህበራት እና የግሉ ሴክተር በከተማዉ ዓመታዊ

1. Without prejudice to the regional government project focus support to the urban centers shall maintain developmental support based on fairness and competition of the urban centers as much as possible; create conducive condition in which they develop and grow rapidly as well.
2. Zonals, especial woreda and woreda administration shall be expected to provide all rounded support to establish and enhance their development by providing the budget and others supports to all urban centers found under them as indicated on sub-article 1 of this article.
3. Without prejudice to sub-article 2 of this article, zonals, especial woreds and woreda administrations shall establish urban centers that are found under them and newly transferred in to urban center by supporting with human resource and material.

## 49. Obligation to Provide Report

Each urban center should present report to the relevant government bodies found in each level on the implementation of the development plan, custom of the budget and audit

## 50. Freedom of the Urban Centers

Every urban center shall have the right to implement powers and duties given in this proclamation which are in line with the constitution and the constitutional system.

## 51. Ensuring Public Participation

1. The urban center residents, civic societies, and private sectors should facilitate

የሥራፕሮግራም፣ በበጀት ረቂቅ፣ በፕሮጀክት ሀሳቦች እና አፈጻጸም፣ በቀጣይ የከተማው ልማት ላይ እንዲወያዩ፣ እንዲከራከሩ እና ሀሳባቸዉንም እንዲገልጹ መድረክ ሊመቻች ይገባል፡፡

2. እያንዳንዱ የከተማ ነዋሪ በከተማው ልማትና መልካም ልማታዊ አስተዳደር ጉዳዮች ላይ የመሳተፍና ከውጤቱም የመጠቀም መብት አለው፡፡
3. ከከተማዉ ነዋሪዎች መካከል የሚወከሉ ለከተማው ሥራ ጉዳይ በተቋቋሙ ኮሚቴዎች ውስጥ እንዲያገለግሉ ሊጋበዙ ይችላሉ፡፡
4. የከተማዉ ህዝብ ለሚያነሳቸዉ ጥያቄዎችና ለሚያቀርባቸዉ አቤቱታዎች ፈጣን ምላሽ ሊሰጥ ይገባል፡፡
5. የከተማው ነዋሪ ሕዝብ በልማትና በጋራ ጉዳዮቻቸው ላይ አጀንዳ የማመንጨትና ለውይይት የማቅረብ መብት አለው፣

meeting to discuss, debate and express their thought on the annual programs of the urban cnter, budget draft, ideas, and implementation of the project, extensional development of the urban center.

2. Each resident of the urban center shall have the right to be a beneficiary of the outcome and to participate on the development and issues of a good developmental governance of the urban center.
3. Delegates from the urban residents may be invited to serve in the committee established for the urban duty affair.
4. Should provide instant response to the inquiries and application to be presented by urban center people.
5. The urban center resident people shall have the right to initiate agenda and present for discussion on development and mutual issues.

## 52. የከተሞች ገቢ

ከተሞች በህግ በተሰጣቸው ሥልጣን መሰረት የራሳቸውን ገቢ የመሰብሰብ፣ ለልማት የማዋል ሥልጣን ይኖራቸዋል፣ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

## 52. Revenue of Urban Centers\

Urban centers shall have the power to collect their income and invest on development in accordance with the power vested on them by law; the details shall be defined by regulation.

## 53. የከተሞች ፋይናንስ አስተዳደር እና የኦዲት ሥርዓት

1. እያንዳንዱ ከተማ ሀብቱን የማደራጀትና የማስተዳደር ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

## 53. Financial Administration and Audit System of the Urban Centers

1. Each urban center shall have powers and responsibilities to organize and administer its resource.

2. በሬጂዮፖሊሲ እና ከፈርጅ አንድ እስከ ሶስት ያሉ ከተሞች ከንቲባው የበጀት ረቂቅ ለምክር ቤቱ አቅርቦ ያስጸድቃል፤ይኸው በጀት የተጠቃለለ የከተማው በጀት ይሆናል፡፡

3. ከንቲባ በሌለባቸው ከተሞች የቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ የበጀት ረቂቅ ለከተማው ቀበሌ ምክር ቤት አቅርቦ ያስጸድቃል፤

4. ከንቲባዉ በየዓመቱ የፋይናንስ ሪፖርት ለከተማው ምክር ቤት ያቀርባል፡፡

5. ከንቲባ በሌላቸው ከተሞች የቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ በየዓመቱ የፋይናንስ ሪፖርት ለከተማው ቀበሌ ምክር ቤት ያቀርባል፡፡

6. አንድ ከተማ የዉስጥ ኦዲተርና ኢንስፔክሽን ሊኖረው ይችላል፤

7. የዉስጥ ኦዲተርና ኢንስፔክሽን ተጠሪነት በሬጂዮፖሊስ፣ ከፈርጅ አንድ እስከ ሶስት ከተሞች ለከንቲባዉ ወይም በፈርጅ አራት እና አምስት ከተሞች ለከተማው ቀበሌ ምክር ቤት ይሆናል፣

8. የዉስጥ ኦዲተርና ኢንስፔክሽን የሃብት አስተዳደሩ በፀደቀዉ የፋይናንስ ደንብ መሰረት መሆኑን በየዕለቱ ያረጋግጣል፡፡

## ምዕራፍ ዘጠኝ
## የቢሮው ሥልጣንና ተግባራት

### 54. የቢሮው ሥልጣንና ተግባራት

ቢሮው አግባብ ባለቸው ሕጎች የተሰጠው ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ከተማ ነክ ሥራዎችንና አፈፃፀማቸውን

2. Ragiopolis and urban centers from category one up to three, the mayor shall submit the budget draft to the council for ratification; this budget shall be a general budget of the urban center.

3. In the urban centers have no mayor, the chief administrator of the kebele shall submit the budget draft to the urban kebele council for approval.

4. The mayor shall submit the finance report to the urbancenter council each year.

5. In the urban centers have no mayor, the chief administrator of the kebele shall submit the finance report to the urban kebele council each year.

6. An urban center may have internal auditor and inspection;

7. The internal auditor and inspection of ragiopolis and urban center from category one up to three shall be accountable to the mayor or the urban centers of category four and five shall be accountable to the urban kebele council.

8. Internal auditor and inspection shall ensure daily if the resource administration is in accordance with the authorized finance regulation.

## CHAPTER NINE
## Powers and Duties of the Bureau

### 54. Powers and Duties of the Bureau

Without prejudice to the powers and duties endow withpertinent laws, the bureau shall have the following powers and duties;

1. Shall have power to examine and approve the

ለማጣራትና ለማረጋገጥ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

2. ለገጠር አገልግሎት ማዕከላት ስኬች ፕላን እንዲዘጋጅላቸው እና አስፈላጊ ባለሙያዎች እንዲኖሩአቸው በማድረግ ወደ ከተማነት እንዲሸጋገሩ ያደርጋል፡፡
3. በከተሞች በየእርከኑ ስለሚኖረው አደረጃጀት ጥናት በማካሄድ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል፣ሲፀድቅም መዋቅሩ እንዲዘረጋ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፡፡
4. ከተሞችን ተስማሚ በሆነ ፈርጅ ለመመደብ የሚያስችሉ መስፈርቶችን በየ3 ዓመቱ በማጥናት ሊከልስ ይችላል፣ሲወሰንም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩት ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆነው ቢሮው ከዚህ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፣

ሀ) የከተሞችን አቅም ለመገንባትና የአካባቢ ልማት ለማፋጠን የሚስችል ጥናት ያካሂዳል፣ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ አተገባበሩንም ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

ለ) ለከተሞች አቅም ግንባታ አስፈላጊ የሆኑ ተቋማት ሊመሰረቱ የሚችሉበትን ሁኔታ እያጠና አግባብ ላለው መንግስታዊ አካል ያቀርባል፣ ያስፀድቃል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣

ሐ) በከተማነት ለመቋቋም የሚቀርቡ የማህበረሰብ ጥያቄዎችን ይመረምራል፣ ውሳኔ ይሰጣል፣

መ) የከተሞችን የፈርጅ ለውጥ ጥናት ያካሄዳል፣ እስከ ፈርጅ 3 የውሳኔ ሃሳብ ለክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት በማቅረብ ያስወስናል፣ ለፈርጅ አራትና ፈርጅ አምስት ከተሞች የደረጃ ለውጥ ውሳኔ ይሰጣል፣

ሠ) የከተማ ነዋሪዎችን የኑሮ ደረጃ ለማሳደግና ከተሞችን ለማዘመን የሚረዱ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ያስፀድቃል፣አፈፃፀሙንምይከታተላል፡፡

activities of the urban connected and their implementation.

2. Effects the rural service centers to be transformed into urban center by preparing sketch plan for and building necessary professionals.
3. Conducting research on the organization found in each level of the urban centers, submit to the executive council of the region for authorization; effect the structure to be developed when ratified; follow up the implementation.
4. May improve criterion to allocate urban centers in the appropriate category by studding in every 3 years; implement up on its approval.
5. Without prejudice to the issues listed in this article, the bureau shall have the following duties;

a) Conducts research to build capacity of the urban centers and to enhance the locality development and to develop the working system; follows up and support the implementation;

b) Studies the condition in which institutions necessary for the urban centers capacity building and submits to the relevant government body to be ratified; follows up the implementation;

c) Examines the inquisitions of the society to be established as urban; provides decision;

d) Conducts research on the change of the urban centers'category; effects up to category 3 to be approved by submitting decision idea to the regional executive council; provides decision of standard change for category four and five urban centers;

e) Conducts research to improve the life standard of the urban center residents and to modernize urban centers and effects to be approved; follows up the implementation.

ምዕራፍ አስር

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

55.ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚረዳ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ቢሮው ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚወጣን ደንብ ለማስፈጸም የሚረዳ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡

56. ተፈፃሚነት የሌላቸው እና የተሻሩ ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሕጎችና አሠራሮች በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

57. አዋጁ የሚፀናበትጊዜ

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል ፡፡

እንዳሻው ጣሰው
የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ፕሬዝደንት
የካቲት 20/2016 ዓ/ም
ወልቂጤ

CHAPTER TEN

Miscellaneous Provisions

**55. Power to Issue Regulation and Directive**

1. The executive council of the region may issue regulation to implement this Proclamation
2. The bureau may issue directive to implement this Proclamation and the regulation to be issued in accordance with sub-article 1 of this article.

**56. Inapplicable and Repealed Laws**

Any law and practices prejudice to this Proclamation shall not be applicable on matters indicated in this Proclamation.

**57. Effective date**

This Proclamation shall enter into force up on the date of its publication in the Negarit Gazeta.

**ENDESHAW TASEW**
**President of the Central Ethiopia Region State**
**February 28/2024**
**Wolkite**